# ነብዩ ሙሐመድ

(ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)

## በመጽሐፍ ቅዱስ

ዝግጅት፡- ዑመር አርሲ

ከእንግሊዘኛ የተረጎመው፡- አቡ የሕያ አማን

2007

የአማርኛው ትርጉም መብት ለአሳታሚው
በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

2007

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

የደራሲው አድራሻ፡-

E-mail: robumer.robe5@gmail.com

የመጀመሪያ ዕትም መጋቢት 2007

# ምስጋና

ምስጋናና ውዳሴ ለአላህ፣ ለኃያሉ አምላክ፣ ለዚያ ስለተወዳጁ ነብያችን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)[1] የተነገሩ ትንቢቶችን ለመላው አንባቢያን በአንድ ቅርጫት ውስጥ እንዳሰባስብና እንዳጠናቅር ላደረገኝ ጌታ የተገባ ይሁን፡፡

ልባዊ ምስጋናዬን ለሁሉም ሙስሊም ምሁራን፣ ለነዚያ ጥልቅ ምርምር ላደረጉትና ስለተከበረው ነብያችን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መገለጫዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ አውጥተው ላደረሱን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡ አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ)[2] ሥራቸውን እንዲቀበላቸውና ሁላቸውንም በጀነት እንዲመነዳቸው እለምናለሁ፡፡

እኔም እነዚህን ትንቢቶች በማጠናቅርበትና በምተረጉምበት ወቅት ለፈጸምኳቸው ማናቸውም ስህተቶች ምህረቱን እንዲለግሰኝ ጌታዬን አላህን እለምናለሁ፡፡

ይህን ካልኩ በኋላ፣ እንደ ውሒብ ዐብዱል ዋሲዕ፣ ዐብደሏህ ኩት፣ ኢብራሂም ሙኽታር፣ ሀምዛ፣ ሙሐመድኑር እና ዐብዱል ቃዲር ሃሺም ያሉ ወንድሞች በርግጥ ባለ ውለታዎቼ ናቸው፡፡ የዚህን መጽሐፍ የአርት ኦት ሥራ በመሥራትና ገና ከጅምሩ የመጽሐፉ ረቂቅ ከተጀመረበት አንስቶ ዝግጅቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ትኩረታቸውን በመስጠት ላበረከቱልኝ ወደር የለሽ አስተዋጽኦ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

---

[1] "ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም" የሚባለው የነብያችን ስም የተወሳ ጊዜ ሲሆን ትርጉሙም "የአላህ ሰለዋት (እዝነት) እና ሰላም በርሱ (በመልዕክተኛው) ላይ ይሁን" ማለት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የርሳቸው ስም ሲወሳ በርሳቸው ላይ ሰለዋትና ሰላምታ ማውረድ በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው፡፡

[2] "ሱብሓነሁ ወተዓላ" የሚባለው የጌታችን የአላህ ስም የተወሳ ጊዜ ሲሆን ትርጉሙም "ጥራትና ልቅና ለርሱ ተገባው" ማለት ነው፡፡ ይህ አላህ ከማንኛውም ጉድለት የጠራና ከሚያጋሩበት ሁሉ የላቀ መሆኑን መሆን ለመግለጽ ነው፡፡

እንደዚሁም በተለይ የሕትመቱን ሂደት ለተከታተሉልኝና ላቀናጁልኝ፣ በተጓዳኝም መጽሐፉን ለማጠናቀቅ ዳግም የአርት ኦት ሥራ በመሥራት ከጎኔ ለቆሙት ለወንድም ሙሐመድና ዐብዱል ሐኪም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ልዩ ምስጋናዬን ለአቶ ገመቹ ሂኒካ፣ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረርና የድሮ ጓደኛዬ፣ ብሎም የዚህ መጽሐፍ የጽሕፈት ሥራ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት የፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ለነበረው፣ ቢዚ ከሆነ ጊዜው ሰዓታትን በመውሰድ ይህን መጽሐፍ በማንበብና አስተያየቱን በመለገስ ላበረከተልኝ አስተዋጽኦ ልዩ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ ይህን መጽሐፍ ለማሳተም በገንዘብ ዕርዳታ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ ወንድሞች፣ እህቶችና ድርጅቶች ልዩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ሁላችንም ከርሱ ምርጥ ባሮች ጋር የዘላለም የደስታ ሀገር የሆነችውን ጀነት እንዲመነዳን እለምናለሁ፡፡ አኋሁምመ ኣሚን …

ዑመር አርሲ

2007

## በአላህ ስም፣ እጅግ በጣም ርኅሩህ፣ በጣም አዛኝ በሆነው፡-

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) የተገባ ይሁን፡፡

*ምስጋና ለዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው፣ ጨለማዎችንና ብርሃን ላደረገው ለአላህ የተገባ ነው፤ ከዚያም እነዚያ የካዱት (ጣዖታትን) በጌታቸው ያስተካክላሉ፡፡ (6፡1-3)*

ጥራትና ውዳሴ ለአላህ የተገባ ይሁን፣ ለዚያን ልጅን ላልያዘው፣ በንግሥናው ተጋሪ ለሌለው፣ በሥልጣን ተካፋይ ለሌለው፣ ከውርደትም ረዳት ለሌለው፣ በአምልኮው አምሳያ ለሌለው፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ (አምልኮ የሚገባው አካል/ኃይል) ከቶ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡

*አላህም ልጅ አለው አለው፤ (ከሚሉት) ጥራት ተገባው፤ አይደለም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው፡፡ ሁሉም ለርሱ ታዛዦች ናቸው፡፡ (አል-በቀራህ 2፡116)*

መሪያችን ሙሐመድም (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ባሪያና የመጨረሻው ነብይ፣ አላህ በቅን መመሪያና በእውነተኛ ዲን የላከው መልዕክተኛው መሆኑን እመሰክራለሁ፡፡

*እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልዕክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ዲን ላይ ከዲን ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው፡፡ (አት-ተውባህ 9፡33)*

የአላህ ሰላም፣ እዝነትና በረከት በመልዕክተኛው፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን፡፡ እንደዚሁም ሰላም እስከ ፍርዱ ዕለት እነርሱን በሐቅ በሚከተሉት፣ በነዚያ በእውነትና በፍትሕ በሚያስተዳድሩት ላይ ይሁን፡፡ በመጨረሻም አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ሥራችንን እንዲቀበለን እለምናለሁ፡፡

# ማውጫ

መግቢያ ........ 7
የመጽሐፉ ባለቤቶች እውነታውን መደበቃቸው ........ 10
የቃል ኪዳኑ ነብይ ........ 13
ሙሴን የሚመስል ነብይ ........ 19
ስለዐረብ የተነገረ ሸክም ........ 24
የጌታ ባሪያ (ኢሳይያስ 42) ........ 26
የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል ........ 37
ታማኙና እውነተኛው፣ እርሱ ማነው? ........ 39
መካን (በካን) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታውቃታላችሁ? ........ 44
መካ ወይስ ጽዮን? (ኢሳይያስ 60፡1-22) ........ 46
ቂብላ በመጽሐፍ ቅዱስና በአል-ቁርኣን ........ 51
ለቂብላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ........ 55
ኢስላማዊው የሐጅ ሥነ-ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስ ........ 57
ካዕባ በመጽሐፍ ቅዱስ ........ 63
አንተስ ታውቀዋለህ? ........ 67
በቅርብ የተገኙ መረጃዎች ........ 78
ማጠቃለያ ........ 83
ዋቢ መጽሐፍት ........ 88

## መግቢያ

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ይሁን፡፡ የአላህ ሰላምና በረከት በሙስጠፋ ላይ፣ በቤተሰቦቻቸው ላይ፣ በባልደረቦቻቸው ላይ፣ እንዲሁም እስከ ዕለተ ትንሳኤው ድረስ የርሳቸውን ፈለግ በሚከተሉት ሁሉ ላይ ይሁን፡፡

የሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነብይነት የማብራራት አስፈላጊነት ዛሬ ኢስላምን በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ነጥብ እየሆነ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከረጅም ጊዜ በፊት የተጠቀሰው መረጃ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በስም እስከ መጥቀስ ድረስ ያለው ሁኔታ በሰባተኛው ክ/ዘመን በሳቸው ለሰው ልጆች መድህን ሆኖ መምጣት እውን ሆኗል፡፡ ቅዱስ ቁርኣንም አሁን ስለተነሳው ጉዳይ እነዚያን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ ሰዎችን እንድንጠይቅ በሚቀጥለው አንቀጽ ያበረታታናል፡፡

*“(ሙሐመድ ሆይ) ወዳንተ ያወረድነውን መልዕክት ከተጠራጠርክ፣ እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን ያነቡ የነበሩ ሰዎችን ጠይቅ፡፡ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በርግጥም መጥቶልሃል፡፡ ስለሆነም ከተጠራጣሪዎቹ አትሁን፡፡” (አል-ቁርኣን 10፡94)*

ስለዚህ፣ ይህ መጽሐፍ የተደበቀውን መረጃ ለሕዝብ ግልጽ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሁሉንም በአንድ ቅርጫት ውስጥ በማስቀመጥም ለመላው አንባቢ ታማኝ መረጃ ያቀርባል፡፡ በርካታ ሙስሊም ምሁራን ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነብይነት የተለያዩ ጎኖችን በመግለጽ የተለያዩ መጽሐፍትን ጽፈዋል፡፡ ይህ መጽሐፍ፣ ሆኖም የሁሉም መጽሐፍ ስብስብ በመሆን ከምንጩ የተገኘ መረጃን በመስጠት ለእውነት ፈላጊዎች የራሱን ግልጋሎት ያበረክታል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን፣ እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የነብይነት ትንቢቶችን አሳማኝ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ

በተሳሳተ መንገድ ለሚተረጉሙት መልካም ምላሽ አለው፡፡ ስለዚህ ከመጋረጃው በስተ ጀርባ ባለው ነገር ላይ አጽንኦት እንስጥ!

ስለ'ኒህ ታላቅ ሰው እውነተኛ የሕይወት ገጽታ ገለልተኛ በሆኑ የተለያዩ ምሁራን በሰጡት አስተያየቶች በከፍተኛ ሁኔታ ተደንቀናል፡፡ እንዲሁም የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻው ክፍል ስለርሳቸው የተሰጡ አስተያየቶችንና ምስክርነቶችን "አንተስ ታውቀዋለህ?" በሚለው ርዕስ ሥር አካቷል፡፡ እነዚህ ምሁራን እ'ኒህን ሰው ታላቅ በማለት አወድሷል፣ ይህም የሆነበት እውነታ እነሱ እነዚያ ወደ እውነትና ዕውቀት ያዘነበሉና በሐቅ ላይ የቆሙ ስለነበሩ ነው፡፡

የነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የነብይነት ትንቢቶች በምንመረምርበት ጊዜ ከርሳቸው ሕይወትና ተልዕኮ ጋር በማዛመድ የነርሱን የአፈጻጸም ሁኔታ ለማየት እንሞክራለን፡፡ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ነብያዊ ትንቢቶች ከርሳቸው ውልደት በፊት የተተነበዩትንና በርሳቸው መምጣት የተፈጸሙትን እንደ ተዛማጅ መረጃዎች ከሕያው ማስረጃ (አል-ቁርኣን) ጋር በማዛመድ በንቃት እንመረምራለን፡፡

ሌላው የክርስቲያኖች የነዚህ ነብያዊ ትንቢቶች ለሌሎች የመተርጎም ሙግት ነው፣ እውነታው ከነርሱ አስተሳሰብ የራቀ ሆኖ ሳለ፡፡ እናም እነሱ እውነታውን ለመረዳት በጥልቀት እንዲያስቡና በምርምር ላይ የተመሠረተ ምንባብ እንዲያደርጉ ሐሳባችንን ለመስጠት እንወዳለን፡፡

ክርስቲያኖች ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከሚያስቡት በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ነብያዊ ትንቢቶች አሉ፡፡ ዛሬ ዛሬ ይህ ጥያቄ ለሙስሊሞችና ለክርስቲያኖች የሚያጓጓና አንገብጋቢ ነገር ሆኗል፡፡ እነሱን "መጽሐፍ ቅዱስ ስለሙሐመድ ምን ይላል?" ብለን በምንጠይቅበት ጊዜ በአሉታዊ

መልኩ እንደሚመልሱ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ነገሩ "ከምንም ነገር በፊት፣ ዓይኖች ከታወሩ፣ አንድ ሰው በልቡ ማየት አለበት፡፡" እንደሚባለው ነው፡፡

በእያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወት ውስጥ ከራስ በላይ የታላቅ ዓላማ እውን ማድረጊያ ጊዜ ይመጣል፡፡ እውነትን መፈለግና ነፍስን ከግቧ ማድረስ በዕውቀት ይጀምራል፡፡ እኛ ማን ነን? ከየት ነን? እንዲሁም ወዴት እየሄድን ነው? እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች ማንም ሰው ለመንፈሳዊ ጠቀሜታው ሲል ቀጥተኛውን መንገድ ለመፈለግ መጠየቅ አለበት፡፡

*"ሁሉም ነገሮች በእውነትና በርኅራኄ ከልብ የሚተገበሩ ከሆኑ፣ የሰው ልጅ ከዛሬው መመሰቃቀል ስቃይ አይደርስበትም ነበር፡፡ እያንዳንዱ ነፍስ ከሁሉም ሕይወት ካላቸውና ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች ጋር አንድ መሆኗን ብታውቅ፣ እነሱ ልቦቻቸውን ይከፍቱና በርኅራኄ ዓይን አንዱ በሌላው ጫማ ይራመዳል፡፡ የብጥብጥና የንዴት ተግባራት በነዚያ በሰላምና በደስታ ተግባራት ይተካሉ፡፡ እኛ አንድ ሕዝብ ነን፣ ለአንድ ዓላማ አንድ የሆንን፣ ዕድገት/መሻሻል እና ፍቅር የአንድነት ኃይል ናቸው፡፡ ቀለል አድርገህ ያዘው፡፡"*[3]

***"እናንተ የሰው ልጆች ሆይ! እኛ በርግጥ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁ ዘንድም ሕዝቦችና ነገዶች አደረግናችሁ፤ በአላህ ዘንድ ከናንተ በላጫችሁ አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ በርግጥ አላህ ሁሉን ዐዋቂ፣ የውስጥ ዐዋቂ ነው፡፡"***

***(አል-ቁርኣን 49፡13)***

[3] አሞን፣ ሰኔ 21, 2003 እ.አ.አ

## የመጽሐፉ ባለቤቶች እውነታውን መደበቃቸው

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) እንዲህ ይላል፡-

***የእስራኤል ልጆች ሆይ! የለገስኳችሁን ፀጋዎች አስታውሱ፡፡ ቃል ኪዳናችሁን ሙሉ፡፡ እኔ ቃል ኪዳኔን እሞላለሁ፡፡ እኔን ብቻ ፍሩኝም፡፡ ከናንተ ጋር ያለውን (መጽሐፍ/ተውራትን) የሚያጸድቅ ሆኖ ባወረድኩት (መጽሐፍ/በቁርኣን) እመኑ፡፡ በውስጡ የያዘውን መልዕክት በማስተባበል የመጀመሪያዎቹ አትሁኑ፡፡ አንቀጾችን ኢምንት በሆነ ዋጋ (ጠፊ በሆነችው የዚህች ዓለም ፀጋ) አትለውጡ፤ እኔን ብቻ ተጠንቀቁም፡፡ እውነትን በእብለት አትሸፍኑ፤ ሐቅን እያወቃችሁት አትደብቁ፡፡ (አል-ቁርኣን 2፡40-42)***

ያን የተደበቀውን እውነታ ለመረዳት፣ ይህን ጉዳይ በምንመረምርበት ጊዜ የናንተን ትዕግስትና ገለልተኛ አዕምሮ በትህትና እንጠይቃለን፤ ምክንያቱም እርሳቸውን እንደራሳቸው ወንዶች ልጆች የሚያውቋቸው ሆነው ሳሉ የእስራኤል ልጆች ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እውነታውን ሆን ብለው ደብቀዋልና፡፡

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) እንዲህ ይላል፡-

***እነዚያ መጽሐፍትን የሰጠናቸው ሕዝቦች (ሙሐመድን) ልጆቻቸውን የሚያውቋቸውን ያህል ያውቁታል፡፡ ከነርሱ ከፊሎቹ እውነትን - እያወቁ - ይደብቃሉ፡፡ ይህ ከጌታህ የተላለፈ እውነት ነው፡፡ ከተጠራጣሪዎቹ አትሁን፡፡ (አል-ቁርኣን 2፡146-147)***

እስራኤሎች ከተከበረው ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ፊታቸውን እንዲያዞሩ ያደረጋቸው የመጀመሪያው ነጥብ የነርሱ ለዓለማዊ (ቁሳዊ) ነገሮች ያላቸው ፍላጎታቸው የበለጠ ማደግ ሲሆን እነርሱን ከዚህ የሚያነቃንቃቸው ነገር እስከማይኖር ደረጃ ድረስ ሂዶ፣ ሌላው ቀርቶ የኃያሉ አምላክ ትዕዛዝ እንኳን፡፡ እናም ለገዛ

ፍላጎታቸው ባሪያ ለመሆን በቁ፡፡ ከዚህ የተነሳ አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) እንዲህ ይላል፡-

***ለሙሳ መጽሐፉን (ተውራትን) በርግጥ ሰጠነው፡፡ ከበኋላቸው መልዕክተኞችን አስከተልን፡፡ ለመርየም ልጅ ዒሳም (ነብይነቱን የሚያረጋግጡ) ግልጽ ተዓምራቶችን ሰጠነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስም አጠነከርነው፡፡ ከስሜታችሁ ጋር የማይጣጣሙ (መልዕክቶችን ይዞ) መልዕክተኛ በመጣላቸውም ቁጥር (ከመከተል) ትኮሩ የለምን? ከፊሎቹን አስተባበላችሁ፤ ከፊሎቹን ደግሞ ገደላችሁ፡፡***

***(አል-ቁርኣን 2፡87)***

***የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! መልዕክተኛችን ከመጽሐፉ ትደብቋቸው ከነበሩት (መልዕክት) ብዙዎቹን ሊገልጽላችሁ (አሁን አስፈላጊ ያልሆኑትን) ብዙዎቹን ደግሞ እንዲሁ ሊያልፋቸው መጥቶላችኋል፡፡ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ ከአላህ መጥቶላችኋል፡፡ አላህ በፈቃዱ በርሱ (መጽሐፍ) የርሱን ውዴታ የሚሹትን ወደ ሰላም መንገድ ይመራቸዋል፡፡ ከጨለማዎችም ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል፡፡ ቀጥተኛውን ጎዳናም ይመራቸዋል፡፡***

***(አል-ቁርኣን 5፡15-16)***

ኑዕማን እብኑ በሺር (ረዲየሏሁ ዐንሁ)[4] ባወሩት ሐዲሥ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡

***"በርግጥ በሰውነት ውስጥ አንዲት ቁራጭ ሥጋ አለች፤ እርሷ ከተበላሸች መላው ሰውነት ይበላሻል፡፡ እርሷ ከተስተካከለችም መላው ሰውነት ይስተካከላል፤ ንቁ! እርሷም ልብ ናት፡፡"***

በዓለም አቀፍ ደረጃ በእምነት መካከል ያለው ግንኙነት ማደግ በርካታ አጋጣሚዎችንና ክርክሮችን ፈጥሯል፡፡ በዚህ

[4] "ረዲየሏሁ ዐንሁ" የሚባለው የሰሓባ (የመልዕክተኛው ባልደረባ) የተወሳ ጊዜ ሲሆን ትርጉሙም "አላህ ሥራውን ይውደድለት" ማለት ነው፡፡

ምክንያት አንዳንድ ጊዜ አዕምሮን እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ፈተናዎችና ጥርጣሬዎች ያጋጥሙታል፡፡ ስለእውነተኛው ዓለም ያለንን የተሳሳተ ግንዛቤ ለማስወገድ ልብ ላይ ጥገኛ መሆን ይኖርብናል፡፡ ይህን ስናደርግ፣ ስለእውነተኛው የኢስላም ነብይ የዓለምን አሉታዊ አመለካከት አንድ ላይ ሆነን ማስወገድ እንችላለን፡፡ ንጹሕ ልብና ጥልቅ አዕምሮ በሃይማኖታዊ ሕይወትህ ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያመጣሉ፡፡ በዚያ አካሄድ በትክክለኛና በስህተት መካከል የመምረጥ ነፃነት አለ፡፡ ይህን በማድረግ ዘላለማዊ ሕይወትን ልታገኝ ትችላል፣ በርግጥ በአላህ ፈቃድ፡፡

ስለተከበረው ነብያችን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መገለጫዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምንወራበት ጊዜ፣ ከመጽሐፉ ባለቤቶች ጋር በልበ ሙሉነት ውይይት ለማድረግ በቂ ማስረጃ አለን፤ ምክንያቱም የተወሰኑ የተረጋገጡ እውነታዎች በመኖራቸው፡፡ ከዚህ ዓለም አቀፋዊ የዘላለም ሕይወት ጥያቄ በምንጀምርበት ጊዜ እኛ እንደ ሙስሊሞች ለነርሱ የተረጋገጡ ማስረጃዎችን በማቅረብ አስተሳሰባዊ ግንዛቤ የመፍጠሪያ ጥልቅ ዕውቀትን መጠቀም ይጠበቅብናል፡፡ ያንን የመጽሐፉ ባለቤቶችን አሉታዊ አመለካከት ወደ አዎንታዊ የሚለውጥ ጭብጥ ማቅረብ ይኖርብናል፡፡ እኛ ስለተከበረው ነብያችን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች መመርመር እንድንችል በአል-ቁርአን ውስጥ ጠቋሚ የሆኑ ማመሳከሪያ ነጥቦች አሉን፡፡ ከነዚህ መካከል በርግጥ የተወሰኑት ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ናቸው፡፡

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ቁርአናዊ አንቀጾችን በሚገባ ማስተዋል የተከበረው ነብያችን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጾች አንፃር ለመተርጎም መሠረታዊ አስፈላጊነት አላቸው፡፡ እነርሱ እውነታውን ለመደበቅ የፈለጉትን ያህል ጥረት ለማድረግ ቢሞክሩና ቢደክሙ፣ እነዚህ መገለጫዎች ከተከበረው የኢስላም ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሕይወት፣ ታሪክ፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ተግባራትና ስብዕና/ማንነት

*ጋር ፍጹም የሚጣጣሙ/ የሚስማሙ እና ከርሳቸው ውጭ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ለሌሎች ነብያት የማይገቡ ናቸው፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢስላም በመጽሐፍ ቅዱስ ላቦራቶሪ ውስጥ ተመሳክሮ የተረጋገጠ መሆኑን ነው፡፡ የመጽሐፉ ባለቤቶች እነዚህን እውነታዎች ለማስተባበል ከደፈሩ፣ ይህ የሚያሳየው እነሱ የገዛ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዳስተባበሉ ነው፡፡ እውነታውን ለመደበቅ የነርሱ ከፍተኛ ጥረት እንዳለ ሆኖ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከዓለም አቀፋዊው የአላህ መልዕክተኛ፣ ያ መላውን የሰው ልጆች ወደ ቀጥተኛው መንገድ መምራት ከሚችለው ኢስላማዊ አስተምህሮ ጋር መረጃን አስተካክሎ ያዛምዳል፡፡*

## የቃል ኪዳኑ ነብይ

እውነታው የሚሽከረከረው ለነብዩ ኢብራሂም (ዐለይሂስ ሰላም) እና ለልጃቸው እስማዔል (ዐለይሂስ ሰላም)[5] በፋራን ተራራና በቄዳር በተገባው የተስፋ ቃል ዙሪያ ነው፡፡ በመጨረሻም እውነታው በኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) አገላለጽ የሚመረመርና የሚደመደም ሲሆን ይህም የርሱ እስራኤሎችን መርገም የሚያመለክተው እነርሱ የአምላክን መንግስት የማቋቋም መብት እንደሚከለከሉ በትንቢት ተረጋግጧል፡፡

***ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- "ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፣ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ፣ ለዓይኖቻችንም ድንቅ ነው የሚለውን ከቶ በመጽሐፍ አላነበባችሁም?"***

***ስለዚህ እላችኋለሁ፣ የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ትወሰዳለች፣ ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች፡፡ በዚህም***

---

[5] "ዐለይሂስ ሰላም" የሚባለው ማንኛውም ነብይ የተወሳ ጊዜ ሲሆን ትርጉሙም "ሰላም በርሱ ላይ ይሁን" ማለት ነው፡፡

*ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፣ ድንጋዩ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጨዋል፡፡ (ማቴዎስ 21፡43-44)*

ይህ የነብይነት ፀጋ ከእስራኤላውያን ወደ እስማዔላውያን መቀየርን እንደሚያመለክት በመላምት ብንይዘው ምን ይሆናል? በርግጥ ይህ መላምት አይደለም፡፡ ነገር ግን እውነታው ይህ ነው፣ ያ ከእስማዔል ዝርያ የመጣ፣ ለዓለማት እንደ ማዕዘን ድንጋይ ሆኗል፡፡ ቀጥሎ ካለው ውብ ሐዲሥ መማር እንደምንችለው እርሱም ለዘላለም የሚኖር ብርሃን ነው፡፡ አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዳወሩትና ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት የተከበረው ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡-

*"የኔ ምሳሌና ከኔ በፊት የነበሩት የቀደምት ነብያት ምሳሌ ልክ በአንድ ሰው እንደተገነባ ቤተ መንግስት ነው፤ በጣም ድንቅና ውብ ሲሆን ለአንድ ብሎኬት የሚሆን ቀዳዳ ከማዕዘናቱ በአንዱ ተወው፡፡ በዙሪያው የሚያልፉ ሰዎች በውበቱ እንዲደነቁ አደረጋቸው፡፡ እናም ግራ በመጋባትና በመደነቅ "ለምንድነው እዚህ ጋ አንድ ብሎኬት ያልተኖረው?" በማለት ይጠይቃሉ፡፡ (እዚህ ጋ ሲደርሱ) የተከበረው ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)፡- እኔ ያ የመጨረሻው የማዕዘን ብሎኬት ነኝ፣ እንዲሁም እኔ የነብያት ሁሉ የመጨረሻ ነኝ" አሉ፡፡*

መረጃዎችን በማመሳከር ስንመረምር እውነታውን ልናገኝ እንችላለን፡፡ ለአብርሃም የተገባው የተስፋ ቃል፣ ያም አምላክ ሁሉንም ሕዝብ በርሳቸው ዝርያ እንደሚባርክ የተናገረው ተፈጽሞ ይሁን አይሁን የሚለውን ስንመረምር ይህ የሚፈጸመው በእስራኤላውያን ወይስ በእስማዔላውያውን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ለምን? ስለኢስላም ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን ለመፈተሽ ስንሞክር በመጽሐፉ ባለቤቶች ሆን ተብሎ የተደበቀውን እውነታ ገሃድ ለማውጣት እየታገልን ነው፡፡

ከክርስቲያኖች “እስማዔል ሕገ-ወጥ ልጅ ነው” እናም እርሱ ከአባቱ ነብይነትን መውረስ አይችልም የሚለውን መስማት ሰልችቶናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይህን የሐሰት ክስ አይደግፍም፡፡ ኢየሱስም (ዐለይሂስ ሰላም) ነብይነት ከእስራኤላውያን ተላልፎ ለሌላ እንደሚሰጥ በትንቢት ተናግሯል፡፡ ይህን ሽግግር ከተስማማንበት ለአብርሃም (ዐለይሂስ ሰላም) የተገባው የተስፋ ቃል ይፈጸም ዘንድ በርግጠኝነት ወደ እስማዔላውያን መሸጋገር አለበት፤ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ምክንያቱም እስራኤላውያን ተበላሽተዋልና፡፡

***ስለእስማዔል ሰምቼሃለሁ፣ እነሆ ባርኬዋለሁ፣ ፍሬያምም አደርገዋለሁ፣ እጅግም አበዛዋለሁ፣ አስራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፣ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ፡፡***

***(ዘፍጥረት 17፡20)***

ተመልከቱ! አብርሃም የመጀመሪያ ልጁን እንዲባርክለት አምላክን ጠይቋል፤ አምላክም ልመናውን ወዲያው ተቀብሎታል፡፡

***ለአንድ ሰው አንዲቱ የተወደደችና አንዲቱ የተጠላች ሁለት ሚስቶች ቢኖሩት፣ ለእርሱም የተወደደችው፣ ደግሞም የተጠላችው ልጆችን ቢወልዱ፣ በኩሩም ከተጠላችው ሚስት የተወለደው ልጅ ቢሆን፣ ለልጆቹ ከብቱን በሚያወርስበት ቀን ከተጠላችው ሚስት በተወለደው በበኩሩ ፊት ከተወደደችው ሚስት የተወለደውን ልጅ በኩር ያደርገው ዘንድ አይገባውም፣ ነገር ግን ከከብቱ ሁለት እጥፍ ለእርሱ በመስጠት ከተጠላችው ሚስት የተወለደው ልጅ በኩር እንደሆነ ያስታውቅ፡፡ የኃይሉ መጀመሪያ ነውና በኩርነቱ የእርሱ ነው፡፡ (ዘዳግም 21፡15-17)***

ክርስቲያኖች አብርሃም (ዐለይሂስ ሰላም) “ሕገ-ወጥ ልጅ” ነበረው ብለው የሚከሱ ከሆነ ይህ የአምላክን ነብይና የበርካታ ነብያትን አባት መስደብ ነው፡፡ እነዚያን አብርሃምን የሚረግሙትን

በተመለከተ አምላክም እነርሱን መልሶ እንደሚረግም ተናግሯል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እርሱን የሚያወድሱትን አምላክም ያወድሳቸል፡፡ እናም ወዮላቸው! ለነዚያ እርሱን ለሚረግሙት! ሙስሊሞች እርሳቸውን አይረግሙም፡፡ ይልቁንም ለሙስሊሞች ከእያንዳንዱ ሶላት በኋላ ቀጥሎ ያለውን ሰላምታ በርሳቸው ላይ ማውረድ የአምልኮአቸው አካል ነው፡-

*“አላህ ሆይ! ሙሐመድንና ቤተሰቦቻቸውን ባርካቸው፤ አብርሃምንና ቤተሰቦቻቸውን እንደባረካቸው ሁሉ፤ በርግጥም አንተ ምስጉን የልቅና ባለቤት ነህ፡፡”*

*የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፡፡ (ዘፍጥረት 12፡3)*

*ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፡፡ (ሮማውያን 3፡23)*

አብርሃምን በመስደባቸው ለክርስቲያኖች ወዮላቸው!!! …

*የችሮታና የአስተውሎት ባለቤቶች የነበሩትን አገልጋዮቻችንን፣ ኢብራሂምን ኢስሐቅንና ያዕቁብንም አስታውስ፡፡ መጭውን ዓለም (ዘውትር) የማስታወስን ልዩ ባህሪ ለገስናቸው፡፡ እነርሱ ከእኛ ዘንድ የተመረጡ ከሆኑት መልካም (አገልጋዮቻችን) ናቸው፡፡ እስማዔልን፣ አል-የሰዕንና ዙልኪፍልንም አስታውስ፡፡ ሁሉም ከመልካም ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን 38፡45-48)*

*የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፣ ቃሌን ሰምተሃልና፡፡ (ዘፍጥረት 22፡18)*

ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት በኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) መምጣት ተፈጽሟል ብለው ይሟገታሉ፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ

እነርሱን አይደግፋቸውም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) በምድር ላይ ለነበሩት ለሁሉም ሕዝቦች የተላከ አልነበረምና፡፡

*እነዚህን አስራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፣ አዘዛቸውም፣ እንዲህም አለ፡- በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፣ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፣ ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ በጎች ሂዱ እንጂ፡፡ (ማቴዎስ 10፡5-6)*

*(ሙሐመድ ሆይ! ለሰው ልጆች) በላቸው፡- "የሰው ልጆች ሆይ! እኔ ወደናንተ - ወደ ሁላችሁም - የተላኩ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ፡፡ የዚያ ሰማያትና የምድር ባለቤትነት የርሱ የሆነው (አምላክ መልዕክተኛ)፡፡ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ያደርጋል፣ ይገድላልም፡፡ በአላህ እመኑ፡፡ በዚያም በአላህና (በተከበረው) ቃሉ በሚያምነው የማይጽፍና የማያነብ መልዕክተኛም (እመኑ)፡፡ ተከተሉትም ትመሩ ዘንድ፡፡" (አል-ቁርኣን 7፡158)*

ይህ በሁለቱ ነብያት መካከል ያለው ልዩነት ነው፡- የመጀመሪያው ለእስራኤላውያን ብቻ የተላከ ሲሆን የኋላኛው ለመላው የሰው ልጆች የተላከ ነው፣ ያ ለአብርሃም (ዐለይሂስ ሰላም) የተገባውን የተስፋ ቃል ያሟላው፡፡ እንዲሁም የማቴዎስ ወንጌል 15፡24 ይመልከቱ፡፡

*እርሱም መልሶ፡- ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ፡፡*

ይህ ትንቢት ለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የማይገባ ከሆነ፣ ለነብዩ አብርሃም (ዐለይሂስ ሰላም) የተገባው የተስፋ ቃል እውን አይሆንም፡፡ ይህ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ጎዶሎ ይሆናል፡፡ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ፈጽሞ የተስፋ ቃል የተገባው ነብይ መሆን አይችልም፤ ምክንያቱም የርሱ ተልዕኮ ለአንድ ሕዝብ ብቻ እንደመሆኑ መጠን፡፡

***የፋራን ተራራ፡-*** ቀጣዩ አስፈላጊው ነጥብና ነገሮችን ለአዕምሮአችን የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው የፋራን ተራራ በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቶች ሲሆኑ እነዚህ ነገሮች ከክርስትናም ሆነ ከእስራኤላውያን የአምልኮ ሥነ-ሥርዓትና መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ጋር ምንም ዝምድና የሌላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ነገር ግን ከኢስላም ጋር በቀጥታ የተገናኙና በእስማኤላውያን የዘር ሐረግ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

***(እስማዔል) በፋራን ምድረ በዳም ተቀመጠ፣ እናቱም ከምድረ ግብጽ ሚስት ወሰደችለት፡፡ (ዘፍጥረት 21፡21)***

የፋራን ተራራ የሚገኘው በመካ፣ በዚያች በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የምትፈለግና የምትወደድ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእስማዔል ልጆች እንደ ቄዳር፣ ቴማን እና ነባዮት ጋር በተያያዘ የተጠቀሱ የተወሰኑ ሌሎች ሃይማኖታዊ ተግባራትም አሉ፡፡

***የሣራ ባሪያ ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደችው የአብርሃም ልጅ የእስማዔል ትውልድ ይህ ነው፣ የእስማዔልም የልጆቹ ስም በየስማቸውና በየትውልዳቸው እንዲህ ነው፣ የእስማኤል የበኩር ልጅ ነባዮት፣ ቄዳር፣ ነብዳኤል፣ መብሳም፣ ማስማዕ፣ … (ዘፍጥረት 25፡12-14)***

***እግዚአብሔር ከቴማን፣ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል፡፡ ክብሩ ሰማያትን ከድኖአል፣ ምስጋናውም ምድሩን ሞልቶአል፣ (ዕንባቆም 3፡3)***

በዚህ ትንቢት ውስጥ ኢስላማዊው የሐጅና ዑምራ የአምልኮ ተግባራት በሁለቱ ቅዱሳን ስፍራዎች፣ መካ (ፋራን ተራራ) እና መዲና (ቴማን) ተተንብየዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው እነዚህ ሁለት

ቅዱሳን ስፍራዎች አላህን በሚያጠሩና በሚያወድሱ ሕዝቦች እንደሚጨናነቁና እንደሚጥለቀለቁ ነው፡፡ እናም ይህ በረካ ነው፡፡

*እግዚአብሔር ከሲና መጣ፣*
*በሴይርም ተገለጠ፤*
*ከፋራን ተራራ አበራላቸው፣*
*ከአእላፋትም ቅዱሳኑ መጣ፤ በስተቀኙም የእሳት ሕግ ነበረላቸው፡፡ (ዘዳግም 33፡1-2)*

ይህ የሚያሳየው የኋላ ኋላ የአምላክ ታላላቅ ነብያት - ሙሴ (ከሲና)፣ ኢየሱስ (ከሴይር) እና ሙሐመድ (ከፋራን ተራራ) (የአላህ ሰላምና በረከት በሁሉም ላይ ይሁንና) መምጣትን/መነሳትን ነው፡፡

በክርስትና ስለአስር ሺህ ቅዱሳን (በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ "አእላፋት ቅዱሳን" የተባለው በእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ "10,000 Saints" ብሎታል)፣ ከፋራን ተራራ ጀምሮ ወደፊት ስላበሩት፣ እንደው ስለነርሱ ምን ታውቃላችሁ? ክርስቲያኖቹ እንዴት ነው የሚተረጉሙት? እኛ በኢስላም በመካ ወይም በፋራን ተራራ ድል ተቀዳጅተው የነበሩ ሙስሊም ሠራዊቶች ቁጥር በትክክል 10,000 ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የ +1 ወይም የ -1 እንኳን ልዩነት የሌለው መሆኑን እናውቃለን፡፡

## ሙሴን የሚመስል ነብይ

*ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርገዋለሁ፣ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀለዋለሁ፡፡ (ዘዳግም 18፡18)*

ይህ ጉዳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ አስፈላጊነቱ በጣም እያደገ የመጣ ጥያቄ እንደ መሆኑ መጠን ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ

ወሰለም) እና ሙሴ (ዐለይሂስ ሰላም) እንዴት እንደሚመሳሰሉ የሚናገረውን ከአል-ቁርኣን አንቀጽን እንድናስቀምጥ ይጠይቀናል፡፡

*እኛ በርግጥ በናንተ ላይ መስካሪ መልዕክተኛን (ሙሐመድን) ላክን፤ (ከዚህ በፊት) ወደ ፊርዖን መልዕክተኛን (ሙሴን) እንደላክን (ሁሉ)፡፡ ፊርዖንም መልዕክተኛውን አመጸ፤ ብርቱ መያዝንም ያዝነው፡፡ (አል-ቁርኣን 73፡15)*

በኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘዳግም 18፡18 ከላይ በርዕሱ "ሙሴን የሚመስል ነብይ" ይላል ....

በብሉይ ኪዳን እንዲህ የሚል ጥቅስ እናገኛለን፡-

*እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሳም፡፡*

*(ኦሪት ዘዳግም 34፡10)*

ሼኽ አሕመድ ዲዳት "መጽሐፍ ቅዱስ ስለሙሐመድ ምን ይላል?" በሚለው መጽሐፋቸው በሦስቱ ነብያት ዙሪያ፡- በሙሴ፣ በኢየሱስ እና በሙሐመድ (በሁሉም ላይ የአላህ ሰላምና በረከት ይሁንና) መካከል የተሟላ ሊባል የሚችል ንጽጽር ሠርተዋል፡፡ ቀጥሎ ያሉት እነዚያ የኦሪት ዘዳግም 18፡18 ትንቢት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መምጣት እንዴት እንደተፈጸሙ በሚገባ የሚያሳዩ ጥቂት አመክንዮዎች (ሎጂኮች) ናቸው፡፡

1. የ12ቱ የእስራኤል ልጆች ወንድማማቾች 12ቱ የእስማዔል ልጆች ናቸው፡፡

2. *"ቃሌንም በአፉ አደርገዋለሁ"* የሚለው የኛን ትኩረት የበለጠ ይስባል፡፡ አል-ቁርኣን በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አፍ ውስጥ እንዴት ሲቀመጥ እንደነበረ

ስንመረምር፣ በዚያ ማንበብም ሆነ መፃፍ የማይችል በሆነው ነብይ፣ ቃል በቃል በመልአኩ ገብርኤል (ዐ.ሰ) አማካኝነት ነበር፡፡ ይህ ቃልም ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ተጠብቆ ይገኛል፡፡

3. *"በስሜም የሚናገረውን"* ይህ ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ማንኛውንም ነገር መናገር ወይም መሥራት ካለባቸው በአላህ ስም ይጀምሩ ነበር፡፡
4. አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ይህን ነብይ የማያዳምጡትን ሙሽሪክ ዐረቦችን ለሚከሰተው ነገር ኃላፊነቱን እንዲወስዱ ነግሮአቸዋል፣ እንዲሁም ተበቅሎአቸዋል፡፡

እስካሁን ድረስ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነብይነት ስለመፈጸሙ ኢስላማዊው አመለካከት እንዴት ጠንካራና ጥልቅ እንደሆኑ አይተናል፡፡ እንደ ክርስቲያኖች በኦሪት ዘዳግም 18፡18 የተጠቀሰውና ሙሴን የሚመስል ነብይ ማን ነበር? ከተባለ ምላሻቸው "ኢየሱስ" ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ከሙሴ (ዐለይሂስ ሰላም) በኋላ ሌላ ነብይ ባለመነሳቱ በኦሪት ዘዳግም የተጠቀሰው ትንቢት ወይ ኢየሱስን (ዐለይሂስ ሰላም) አሊያም ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነው የሚያመለክተው፡፡ አሁን ለምን ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) መሆን እንደማይችል በብልሃት ማረጋገጫ እንፈልጋለን፡፡

ለሁለቱም ሃይማኖታዊ ቡድኖች ይህ ጉዳይ የክርክር ዋናው ነጥብ ሆኗል፣ በዚህ ውስጥ ተከራካሪዎቹ ለአመለካከቶቻቸው ታማኞች ናቸው፡፡ እንደዚሁም በነርሱ አመለካከት ክርክሩን ማሸነፍ ማለት አንድም ተቃራኒውን በማግባባት የነርሱ የመከራከሪያ ነጥብ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ወይም የተቃራኒ ወገን የመከራከሪያ ነጥብ ስህተት መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ እውነታውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአመክንዮና በብልሃት ማግኘት ይቻላል፡፡ በዮሐንስ

ወንጌል ውስጥ የቀረቡ ማስረጃዎች የሙስሊሞች የመከራከሪያ ነጥብ ትክክል መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

***አይሁድም፡- አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፣ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው፡፡ መሰከረም፣ አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ፡፡ እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት፡፡ አይደለሁም አለ፡፡ ነብዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ፡፡ (ዮሐንስ 1፡19-21)***

የማመሳከሪያ ነጥቦችን በመያዝ መጽሐፍ ቅዱስን ብንመለከት በዮሐንስ 1፡21 ውስጥ "ነብዩ" የሚለው ቃል በኦሪት ዘዳግም 18፡15 እና 18፡18 የተጠቀሰውን ትንቢት እንደሚያመለክት በህዳጉ ውስጥ ከሰፈሩ ጽሑፎች ማግኘት እንችላለን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ (ዐለይሂስ ሰላም) በኦሪት ዘዳግም 18፡18 ውስጥ የተጠቀሰው ነብይ አለመሆኑን ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን፤ ምክንያቱም ዮሐንስ ኤሊያስ አይደለም፣ እንደዚሁም ያ በኦሪት ዘዳግም 18፡18 ውስጥ የተጠቀሰው ነብይም አይደለም፡፡ (እባካችሁ በኒው ስታንደርድ ቨርዥን ስተዲ ባይብል፣ ኒው ስታንደርድ ቨርዥን 1፡21፣ ገጽ 1594 ላይ በህዳጉ የሰፈሩ ጽሑፎችን ይመልከቱ)

***አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ አንተ ያለ ነብይ ያስነሳልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ፡፡***

***(ዘዳግም 18፡15)***

ለማስተያየት ያመቻችሁ ዘንድ ይመጣሉ ተብለው የሚጠበቁ ሦስት ሰዎች ነበሩ፡- ክርስቶስ/መሲሕ፣ ኤሊያስ እና ነብዩ (ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ የሆነ)፣ ያ በኦሪት ዘዳግም 18፡18 ውስጥ የተጠቀሰ የሆነው ነብይ ነው፡፡ የኦሪት ዘዳግም 18፡18 ትንቢት ክርስቶስን የሚያመለክት ከሆነ አይሁዳውያን መሪዎች መጠየቅ ያለባቸው ስለሁለቱ ሰዎች (ክርስቶስ እና ኤሊያስ) ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን

እነርሱ አልፎ በመሄድ ስለሦስተኛው ሰው፣ ያ በኦሪት ዘዳግም 18፡ 18 ስለተጠቀሰው ነብይ ጠይቀዋል፡፡ አሁንም ያ ነብይ ኢየሱስ መሆን አለበት የሚል አመለካከት ካለ ይህን ያመለክታል፡- “እንደማያዳምጥ ሰው ማንም ደንቆሮ የለም፡፡” (የአይሁዶች አባባል)

*“እውነት ሁሉ ሦስት እርከኖችን/ደረጃዎችን ያልፋል፡፡ የመጀመሪያው መሳለቂያ መሆን፣ ሁለተኛው የኃይል ተቃውሞ ማስተናገድ፣ እንዲሁም ሦስተኛው እርከን/ደረጃ ራሱን በራሱ በቂ ማስረጃ ሆኖ መቀበል ናቸው፡፡”*[6]

ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሦስቱንም እርከኖች አልፈዋል፡፡ በክርክር ውስጥ ያለው ጉዳይ የበለጠ ቀና እንዲሆን አሁን የተወሰኑ ቀላል ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እንወዳለን፡፡ ያ በዮሐንስ 1፡21 የተጠቀሰው ነብይ ስሙ ማነው?

1. ስሙ ያልተጠቀሰው ለምንድነው?
2. እርሱ ከሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ውጭ ሌላ ከሆነ ያ ነብይ መጥቷል ወይ?

ካልመጣ ክርስቲያኖች የርሱን መምጣት እየተጠባበቁ ናቸውን? እኛ አንዴ ይህ ነብይ በኦሪት ዘዳግም 18፡18 የተጠቀሰው ስለመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ የግርጌ ማስታወሻ ካወቅን እርሱ እንደ ዮሐንስ ምስክርነት ከሆነ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) መሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ሦስቱም የተለያዩ አካላት በዝርዝሩ ውስጥ ተጠቅሷልና፡፡ ቀጥሎ ካሉት ሦስት አማራጮች አንዱ በክርስቲያኖች ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡-

1. አንድ የተወሰነ ሰው መምጣት ካለበት እርሱን መቀበል አለባቸው፡፡

---

[6] አርተን ሾፐንሀር (ጀርመናዊ ፈላስፋ፣ 1788-1860)

2. ምናልባት እርሱ ወደፊት ይመጣል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ይህ ከነርሱ እምነት ጋር ይጋጫል፤ ምክንያቱም እንደነርሱ እምነት ከኢየሱስ በኋላ መንገድ የለምና፡፡
3. እርሱ የማይመጣ ከሆነ፣ አሁንም መጽሐፍ ቅዱስን እውነት ያልሆነውንና የማይፈጸምን ትንቢት በመናገሩ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ይሆናል፡፡

ዛሬ ያ ሙሴን (ዐለይሂስ ሰላም) የሚመስል ነብይ፣ እንደ ኦሪትና ወንጌል ፈጽሞ ያልመጣው፣ ስሙ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሆነው፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት የሚያሟላው ነብይ በአል-ፉርቃን መሠረት መጥቷል፡፡

## ስለዐረብ የተነገረ ሸክም

*ስለ ዓረብ የተነገረ ሸክም፡፡ የድዳናውያን ነጋዴዎች ሆይ፣ በዓረብ ዱር ውስጥ ታድራላችሁ፡፡ በቴማን የምትኖሩ ሆይ፣ ወደ ተጠሙት ሰዎች ውኃ አምጡ እንጀራ ይዛችሁ የሸሹትን ሰዎች ተቀበሉአቸው፡፡ ከሰይፍ፣ ከተመዘዘው ሰይፍ ከተለጠጠውም ቀስት ከጽኑም ሰልፍ ሸሽተዋልና፡፡ ጌታ እንዲህ ብሎኛልና፡- እንደ ምንደኛ ዓመት በአንድ ዓመት ውስጥ የቄዳር ክብር ሁሉ ይጠፋል፣ ከቀስተኞች ቁጥር የቀሩት የቄዳር ልጆች ኃያላን ያንሳሉ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ተናግሮአልና፡፡*

*(ኢሳይያስ 21፡13-17)*

ይህ ትንቢት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እና በባልደረቦቻቸው ከመካ (ከቄዳር) ስደትና በመዲና (ቴማን) ሕዝቦች ተቀባይነት፣ እነዚያ ሁልጊዜ በታዋቂ ስማቸው በሚታወሱት “መሃጂሩን (ስደተኞች)” እና “አንሳር (ረዳቶች)” በቅደም ተከተል ተፈጽሟል፡፡ በተጨማሪም ስለበድር ጦርነት፣ በኢስላም ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ወሳኝ ስለሆነው ጦርነት ይናገራል፡፡ የመካ ሁኔታ በጣም አሰቃቂ ሲሆን፣ ከኢስላም ጠላቶች

ጋር ጠላትነቱ ሊመለስ የማይችልበት ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ ወደ መዲና ስደት ታዘዙ፡፡ ቄዳር እና ቴማን የእስማዔል (ዐለይሂስ ሰላም) ልጆች ስሞች ናቸው፣ ***ከኦሪት ዘፍጥረት 25፡12-13*** ማየት እንደሚቻለው፡፡ የመዲና ነዋሪዎች ነብዩን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እና ባልደረቦቻቸውን በሞቀ ሁኔታ ተቀበሏቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከአንድ ዓመት በኋላ፣ ሙስሊሞች እና ሙሽሪኮች በበድር ሜዳ ጦርነት አካሂዱል፡፡ ሙስሊሞችም በመካ ሙሽሪኮች ላይ ድል በመቀዳጀት ጦርነቱ ተጠናቋል፡፡

"የበድር ጦርነት፣ ቅዳሜ ዕለት፣ ማርች 3፣ 624 ዓ.ል (ረመዷን 17፣ 2 ዓ.ሕ በኢስላማዊው አቆጣጠር) በምዕራባዊ ዐረቢያ ሒጃዝ ክልል (የዛሬዋ ሳዑዲ ዐረቢያ)፣ በኢስላም የመጀመሪያው ቀናት ወሳኙ ጦርነት በሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ትግል መካ ውስጥ ካሉ ባላንጣ ቁረይሾች ጋር በአዲስ መልክ ነበር የተካሄደው፡፡ ጦርነቱ በኢስላም ታሪክ ውስጥ እንደወሳኝ ድል የሚታይ ሲሆን ለመለኮታዊ እገዛ ጣልቃ ገብነት መለያ ነበር፡፡ ወይም ከዓለማዊ ምንጮች አንፃር ለሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስቴራቴጃዊ ጉብዝና ትልቅ ማሳያ ነበር፡፡ በድር በተለይ አል-ቁርኣን ውስጥ ከተጠቀሱ ጥቂት ጦርነቶች አንዱ ነው፡፡ ስለበድር ጦርነት ከፍተኛው ዕውቀት በጊዜው ከነበረው ኢስላማዊ ባህላዊ ሪፖርት ከሁለቱም፣ ከሐዲሥና ከነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሕይወት ታሪክ፣ ከጦርነቱ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በጽሑፍ መልክ ከተመዘገቡት ይገኛል፡፡

ከጦርነቱ ቀደም ብሎ፣ በኋላኛው 623 እና በመጀመሪያው 624፣ ሙስሊሞችና መካውያን በርካታ አነስተኛ ግጭቶችን አካሂዱል፣ የሙስሊም ገዛዋት (በነብዩ የተመሩ ዘመቻዎች) በተደጋጋሚ እንደ መከሰታቸው መጠን፡፡ ሆኖም ግን በድር በሁለቱም ኃይላት መካከል ታላቅ ተሳትፎ የተደረገበት የመጀመሪያው ነበር፡፡ ጠንካራ የመከላከል ቦታ አያያዝ ላይ

በመብለጥ የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ኃይል፣ ያ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጸው፣ የመካውያን መስመሮች ሰበረ፡፡ በርካታ የቁረይሽ ወሳኝ ሰዎችን የገደሉ ሲሆን ቀንደኛውን የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ባላንጣ ዓምር ኢብን ሒሻም ጭምር ተገድሏል፡፡ ለቀደምት ሙስሊሞች እነርሱ በመካውያን መካከል ያሉ ጠላቶቻቸውን የኋላ ኋላ እንደሚያሸንፉ ጦርነቱ የመጀመሪያው ምልክት ነበር፡፡መካ በዚያን ጊዜ ዐረቢያ ውስጥ ካሉ ከተሞች በጣም ሀብታምና ኃያላን ከነበሩ ከተሞች አንዷ ነበረች፡፡ ከዚያ የሙስሊሞችን ሦስት እጥፍ የሚበልጥ ሠራዊት አሰማሩ፡፡ የሙስሊሞች ድልም ሌላ ኃይል በዐረቢያ መነሳቱን ለሌሎች ጎሳዎች ፍንጭ ሰጥቷል፡፡ እንደዚሁም የሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ለነዚያ በመዲና ብዙ ጊዜ ለተበታተነ ማህበረሰብ የመሪነት ቦታን አጠንክሯል የሚል የታሪክ ምስክርነትን አስፍሯል፡

## የጌታ ባሪያ (ኢሳይያስ 42)

***እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፣ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ፣ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል፡፡ አይጮኽም፣ ቃሉንም አያነሳም፣ ድምጹንም በሜዳ አያሰማም፡፡ የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጤስንም ክር አያጠፋም፤ በእውነት ፍርድን ያወጣል፡፡ በምድርም ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፤ አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ፡፡ ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፣ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያጸና፣ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ እስትንፋስን፣ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፣ እጅህንም እይዛለሁ፣ እጠብቅህማለሁ፣ የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ፣ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ፡፡ (ኢሳይያስ 42፡1-8)***

ስለተከበረው ነብያችን፣ ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነብይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተደበቁት መገለጫዎች መካከል የኢሳይያስ 42 ትንቢት ከአል-ቁርኣንና ከሐዲሥ ጠንካራ ድጋፍ አለው፡፡ ከነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስብዕና/ባህሪያት ጋር ይስማማል፡፡ እንዲሁም ከርሳቸው ከእርከን ወደ እርከን ተልዕኮዎች ጋር፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን ጨምሮ ይገጣጠማል፡፡ ይህን ትንቢት በተመለከተ፣ እብን አል-ቀይም ሐሳባቸውን ሰጥቷል፡-

*"ይህ መገለጫ ከሙሐመድ እብን ዐብደሏህ በስተቀር ለሌላ ለማንም ሊስማማ/ሊገጥም አይችልም፡፡ በምድር ላይ ያሉት የሰው ልጆች ሁሉ ቢሰበሰቡ እነዚህን ሁሉ ስብዕናዎች ያለውን አንድም ነብይ መጥቀስ አይችሉም፡፡"*[7]

የዚህ ትንቢት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መፈጸምን በምንመረምርበት ጊዜ ሌላው ጠቃሚው ነጥብ ክርስቲያኖች ለናዝሬቱ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ይገባል የሚሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን፡፡ ይህ ትንቢት ከኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ጋር እንደማይሄድ በማስረጃ ውድቅ ማድረግ እንችላለን፡፡ የመጨረሻ ውሳኔያችንን ለመስጠት ከዚህ ትንቢት አንፃር የሁለቱንም ነብያት (ዐ.ሰ) ተልዕኮዎች በጥንቃቄ ማጥናት አለብን፡፡

አጣዕ እብኑ የሳር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዳለው እኔ ዐብደሏህ እብን ዓምር እብን አል-ዓነስን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) አገኘሁትና ጠየቅኩት፡-

*"ስለአላህ መልዕክተኛ (መገለጫ) እነዚያን በተውራት ውስጥ ስለተጠቀሱት ስብዕናዎች ንገረኝ አልኩት፡፡ እርሱ መልሶ፡- "አዎ! በአላህ እምላለሁ፣ እርሱ በተውራት ውስጥ ተጠቅሷል፣ በአል-ቁርኣን*

---

[7] የሙሐመድ ነብይነት እውነት ወይስ አፈ-ታሪክ፣ ገጽ 207

*ከተጠቀሱትና ቀጥሎ ካሉት መገለጫዎቹ ጋር፡- "ነብይ ሆይ! እኛ መስካሪ፣ አብሳሪ፣ እንዲሁም አስጠንቃቂ፣ ለመሃይማንም ጠባቂ አድርገን ላክንህ፡፡ አንተ የኔ ባሪያና መልዕክተኛ ነህ፡፡ እኔ "አል-ሙተወኪል" (ማለትም በአላህ ላይ ተመኪ) ብዬ ሰይሜሃለሁ፡፡ አንተ ፈጽሞ ጋጣወጥ፣ ኃይለኛ አይደለህም፣ በገበያዎች ብጥብጥ ፈጣሪም አይደለህም፣ አንተ በነዚያ ባንተ ላይ ክፋት በሠሩት ላይ ክፉ አትሠራም፣ ግና አንተ እነርሱን በይቅር ባይነትና በእዝነት ትይዛቸዋለህ፡፡ አላህ እርሱን እንዲሞት አያደርግም፣ የጠመሙ ሕዝቦች "ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም" በማለት ቀጥ እስኪሉ ድረስ፣ በዚያ የታወሩ ዓይኖችን፣ የተደፈኑ ጆሮዎችንና የታሸጉ ልቦችን እከፍትበታለሁ፡፡"[8]*

እኛ ከክርስቲያኖች የዚህ ትንቢት አተረጓጎም ጋር እንግዳ አይደለንም፡፡ እነርሱ ለኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) የተነገረ ነው ብለው ይሟገታሉ፡፡ በርግጥ እኛም ሁለቱም ነብያት ባይላኩና ተልዕኮዎቻቸውም ለዓለም ባይደርስ ኖሮ እንስማማ ነበር፡፡ መልካም ነገሩ ያ ነው - ሁለቱም መጥቷል፣ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ባህሪያት ጋር በአካል ታይተዋል፡፡ ዓለምም ለሁለት ታላላቅ ሃይማኖታዊ ካምፖች ለመከፈል የቻለችው በነርሱ መምጣት ነበር፣ በርግጥ በነርሱ ምክንያት ሳይሆን፡፡ ዛሬ ዛሬ ከላይ በተመለከትነው ትንቢት ማነው በሚገባ የተነገረለት የሚለውን ለመለየት በነርሱ ውብ ታሪክ ላይ ቆመናል፡፡ እንደዚሁም ቀጥሎ ካለው ትንቢት ጋር በማዛመድ በሁለቱ ነብያት መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ቀላል ማሳያዎችን እንጠቀማለን፡፡

1. በአል-ቁርኣን መሠረት ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ባሪያ ናቸው፡፡

[8] ሰሒሕ ቡኻሪ፣ 3፡335

*ያ ፉርቃንን (እውነትን ከውሸት የሚለይ) በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይሆን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው፡፡ (አል-ቁርኣን 25፡1)*

2. እንደ ክርስቲያኖች እምነት ከሆነ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ጌታ እንጂ ባሪያ አይደለም፡፡

   *ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሳት የተነሳ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው፣ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ (ሮሜ 1፡1-4)*

   (ጌታ የጌታ ባሪያ ወይም ጌታ የራሱ ባሪያ መሆን ይችላልን?)

3. እንደ አል-ቁርኣን አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ነብዩ ሙሐመድን እና ኢየሱስን (በሁለቱም ላይ የአላህ ሰላምና በረከት ይስፈንና) ረድቷቸዋል፡፡

*አላህ (መልዕክተኛውን) በዚህችም በመጭውም ዓለም አይረዳም የሚል ግምት ያለው ወደ ሰማይ ገመድ ይዘርጋና ይታነቅ፡፡ አድራጎቱ የሚያስቆጨውን ነገር ያስወግድ (ቁጣውን ያበርድለት) እንደሆነም ይመልከት፡፡ (አል-ቁርኣን 22፡15)*

ከሀዲያን እርሳቸውን ለመግደል አሴሩ፣ አንድ የፊት ጥርሳቸውን ሰብረዋል፣ ፊታቸውንም አቁስለዋቸዋል፡፡ እርሳቸው ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነውን ሰው ገድሎባቸዋል፡፡ እርሳቸውን ለማጥፋትም ሠራዊታቸውን አንቀሳቅሰዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው፣ አላህ፣ ኃያሉ አምላክ ለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይ ወሰለም) በነርሱ ላይ የበላይነትን የሰጣቸው ጊዜ ይቅርታ አደረጉላቸው፣ ምሕረትም ለገሱዋቸው፡፡ ከኢስላማዊ አመለካከት አንፃር፣ ኢየሱስን (ዐለይሂስ ሰላም) ወደራሱ ያነሳው

ጊዜ አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) እውነተኛውን ኢየሱስን (ዐለይሂስ ሰላም) ረድቷል፡፡ *ነገር ግን የክርስቲያኖቹ ኢየሱስ፣ ያ እነሱ የኛ ጌታ ነው ብለው የሚሟገቱለት ቀጥሎ ካሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ማረጋገጥ እንደሚቻለው አልተረዳም፡፡*

ሀ. “በጣም ከባድ” *(ማቴዎስ 26፡37)፡-*

***(ኢየሱስም)፡- ወዲያ ሄጄ ስጸልይ ሳለ በዚህ ተቀመጡ አላቸው፡፡ ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ <u>ሊያዝን ሊተክዝም ጀመር</u>፡፡***

ለ. “እስከሞት የሚያደርስ ጭንቀት” *(ማቴዎስ 26፡38)፡-*

***ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፡፡***

እስካሁን ከላይ የተዘረዘሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች *“ደግፌ የያዝኩት”* በማለት የተገባውን የተስፋ ቃል አይደግፉም፡፡

4. “የተመረጠው” ማለትም “አል-ሙስጠፋ” ሌላው የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስም ነው፡፡

5. በኢሳይያስ 42፡4-6 የተተነበየለት ኢስላማዊ ሃይማኖት ሙሉነትና ዓለም አቀፋዊነት አለው፤ ምክንያቱም የኢስላም ነብይ በአል-ቁርኣን እንደተጠቀሰው ለመላው ዓለም የተላኩ ናቸውና፡፡

***በምድርም ፍርድን እስኪ ያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፣ አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ፡፡ ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፣ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያጸና፣ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ እስትንፋስን፣ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ***

*ጠርቼሃለሁ፣ እጅህንም እይዛለሁ፣ እጠብቅህማለሁ፣ የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ፣ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ፡፡ (ኢሳይያስ 42፡4-8)*

*(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማት እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም፡፡ (አል-ቁርኣን 21፡107)*

በሌላ አንቀጽም የኢስላም ሙሉነት እንደሚከተለው ተጠቅሷል፡-

*ዛሬ እነዚያ የካዱት ከሃይማኖታችሁ ተስፋ ቆርጠዋል (ሊበርዙትና ሊከልሱት፣ ብሎም ሊያጠፉት እንደማይችሉ ተረድተዋል)፡፡ እነርሱን አትፍሯቸው፡፡ እኔን ብቻ ፍሩኝ፡፡ ዛሬ ዲናችሁን (የሕይወት መመሪያችሁን) ሞላሁላችሁ፡፡ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለናንተም ከሃይማኖት (ሁሉ) ኢስላምን መረጥኩ፡፡ (አል-ቁርኣን 5፡3)*

ይህ በትክክል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ከዚህ ጥቅስ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነው፡-

*በምድርም ፍርድን እስኪ ያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፣ አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ፡፡*

ከላይ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ኢየሱስን (ዐለይሂስ ሰላም) አይገልጽም፤ ምክንያቱም ከሚቀጥለው ጥቅስ ማየት እንደምንችለው እርሱ ተልዕኮውን ከማጠናቀቁ በፊት ዓለምን በድንገት ለቋል፡፡

*የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፣ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ የመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡ (ዮሐንስ 16፡12-14)*

ይህ የሚያሳየው የኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ተልዕኮ በርሱ ጊዜ አልመሟላቱን ሲሆን እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ እርሱ ለአሕዛብ (አይሁድ ያልሆነ) የተላከ ሳይሆን ግና ለእስራኤል ልጆች ብቻ የተላከ ነበር፡-

*በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፣ (ሉቃስ 1፡33)*

ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) በያዕቆብ ቤት ላይ እንዲነግስ ከተላከ፣ ለመላው ዓለም በርሱ እንደ አዳኝ ማመኑ ትርፉ ምንድነው?

ክርስቲያኖች ነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ያስተባበሉ ጊዜ በርሱ ላይ ያማረሩት እርሱ ተዋጊ ነው በሚል ክስ ነው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስም የሚቀጥለውን ይጠቅሳሉ፡-

*እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ክፉውን አትቃወሙ፣ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያውን ደግሞ ተውለት፣ (ማቴዎስ 5፡39-40)*

የኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) የማንነት መረጃዎች እርሱ ስለራሱ የተናገራቸው ብቻ ናቸው፡፡ እርሱ መጽሐፍ አልፃፈም፣ ሠራዊትን አልመራም፣ ፖለቲካዊ ቢሮ አልያዘም፣ ወይም ሀብት አላፈራም፡፡ እርሱ ከሞላ ጎደል በመንደር ውስጥ በመቶ ማይሎች ነበር የተጓዘው፡፡ በርሱ ቀስቃሽ ቃላትና ማራኪ ሥራዎች የተደነቁ ሰዎችን ብቻ ነበር መሳብ የቻለው፡፡ የተስፋ ቃል የተገባው መልዕክተኛ በተግባር ጦርነትን በማካሄድና በጠላቶቹ ላይ የድል አድራጊነትን ባህሪ በመጎናጸፍ በሚቀጥለው ጥቅስ እንደተተነበየው ትንቢቱን ፈጽሟል፡-

*እግዚአብሔር እንደ ኃይል ይወጣል እንደ ሰልፈኛም ቅንዓትን ያስነሳል፤ ይጮኻል ድምጹንም ያሰማል፣ በጠላቶቹም ላይ ይበረታል፡፡ (ኢሳይያስ 42፡13)*

ከላይ ያለውን ጥቅስ ለኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም)፣ ለዚያ በጠላቶቹ ላይ አንዲት ድንጋይ እንኳን ላልወረወረው መተርጎም - ከዚህ የበለጠ ሹፈት አለን?

እንደ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ማንም ጀግና የለም፡፡ እርሳቸውም እንዲህ ይላሉ፡-

*"በዚያ ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፣ በአላህ መንገድ ላይ መገደልን እወዳለሁ፣ ከዚያም (ከሞት) መቀስቀስን፣ ከዚያም (እንደገና) መገደልን፡፡"[9]*

*6. በተቀረጹትም ምስሎች የሚታመኑ፣ ቀልጠው የተሠሩትንም ምስሎች፡- አምላኮቻችን ናችው የሚሉ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፣ ፈጽመውም ያፍራሉ፡፡*

*(ኢሳይያስ 42፡17)*

አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ባወሩት ሐዲሥ የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

"አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) እንዲህ ይላል፡-

*"እነዚያ የኔን ፍጥረት አምሳያ ለመፍጠር ከሚሞክሩት በላይ ማን በዳይ አለ? እስቲ አቶምን ይፍጠሩ፡፡ ወይም የስንዴ ፍሬን ይፍጠሩ፡፡ ወይም የገብስ ፍሬን ይፍጠሩ፡፡"*

*(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)*

---

[9] ሙሐመድ፣ አንተ ልክ እርሱን እንደምታየው፣ ገጽ 46

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ)፣ በዚህ ሐዲሥ ቁድሲ በመልዕክተኛው፣ በሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንደበት በኩል እንዲህ ይለናል፡- ከነዚያ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ምስል ከሚሠሩ ሰዎች በላይ ማንም በዳይ የለም፣ ከነዚያ በመፍጠሩ ሚና አላህን (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ለመምሰል ከሚፈልጉት፡፡ ከዚያም እርሱ (ሱብሓነሁ ወተዓላ)፣ ኃያሉ አምላክ፣ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ የሆነው፣ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ይፈትናቸዋል፡፡ ከርሱ ፍጥረት በዓይን ከሚታዩት በጣም ትንሹንና በጣም አነስተኛ የሆነውን ሕይወት ያላቸውን ነገሮች እንዲፈጥሩ - ያ አቶም ይሁን፣ ወይም ከዕፅዋት ነገሮች በጣም ቀላሉን እንዲፈጥሩ - እንደ ስንዴ ፍሬ ወይም የገብስ ፍሬ ያሉትን እንዲፈጥሩ ያዛቸዋል፡፡ እርሱ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ይህን ያደረገው የነርሱን ደካማነትና ውስን ችሎታቸውን ለማጋለጥ ነው፡፡

***"የተቀረጸውን ምስል የሚሠሩ ሁሉ ከንቱዎች ናቸው፣ የወደዱትም ነገር አይረባቸውም፤ ምስክሮቻቸውም አያዩምና አያውቁም፤ ስለዚህ ያፍራሉ፡፡ አምላክን የሠራ ወይስ ለማንም የማይረባ ምስልን የቀረጸ ማን ነው?" (ኢሳይያስ 44፡9-11)***

በሰባተኛው ስብሰባ (ኦክቶበር 13፣ 787) ሁለተኛው የኒቂያ ጉባኤ ቅዱሳን ምስሎችን ማክበርን/ማምለክን በተመለከተ እምነት ነክ አዋጅ አውጥቷል፡፡ http://en.wikipedia.org/wiki/File:Ayasofya Iznik 902.jpg "ያ ቅዱስና ሕይወት ሰጪ መስቀል የትም እንደምልክት እንደመቀመጡ መጠን፣ ልክ እንደዚሁ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን መላእክት ምስሎች፣ እንዲሁም የነዚያ የቅዱሳንና ሌሎች ፃድቃንና ብፁዓን ሰዎች ምስሎች በቅዱሳን ዕቃዎች፣ በስጋጃዎች፣ በታቦት አልባሳት፣ ወዘተ አመራረት ላይ እንዲካተቱ፣ እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ግድግዳዎች፣ በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ፣ እንደዚሁም በጉልህ በሚታዩ ሁሉም ቦታዎች፣ በመንገድ ዳርና የትም፣ በሁሉም እነርሱን በሚያዩት እንዲወደሱ/እንዲመለኩ ዘንድ እንዲቀመጡ ተወስኗል፡፡"

7. ***ምድረ በዳውና ከተሞቹ፣ የቄዳርም ሰዎች የሚቀመጡባቸው መንደሮች ድምፃቸውን ያንሱ፤ (ኢሳይያስ 42፡11)*** የመካ ነዋሪዎች የተደሰቱት በኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ወይስ በሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)? የቄዳር ሕዝቦች የመጀመሪያዎቹ ዐረቦች ናቸው፡፡ እነርሱ የዛሬዎቹ ሳዑዲዎችና የመናውያን ናቸው፡፡ እናም እነዚህ 100% ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ስለዚህ "የአሕዛብ መብራት" እና "የቄዳር ሕይወት ኖረ" የሚሉት ግልጽ ትንቢቶች ለመለኮታዊውና ለእውነተኛው የኢስላም ሃይማኖት ምልክቶች ናቸው፡፡"[10]

8. ***እናንተ ደንቆሮዎች ስሙ፤ እናንተም ዕውሮች ታዩ ዘንድ ተመልከቱ፡፡ ከባሪያዬ በቀር ዕውር ማን ነው? እንደምልከው መልዕክተኛዬስ በቀር ደንቆሮ የሆነ ማን ነው? (ኢሳይያስ 42፡18-19)***

ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንደ ባሪያና ያ የተስፋ ቃል የተገባው መልዕክተኛም ዕውቅና ተሰጥቶታል፡፡

የነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ንጽጽራዊ አስተያየት ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ያልተማሩ መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ አል-ቁርኣን የተገለጸው በጣም በበለጸገ ቋንቋ ነው፡፡ ዐረቦች በዐረብኛ ቋንቋ በጣም ጥሩ ተናጋሪዎች በሆኑበት ጊዜ፣ ለዚያም በጣም ይታወቁ በነበሩበት ወቅት፣ እንዲሁም በሥነ-ግጥም ጠንካራዎች በሆኑ ጊዜ ነበር የተገለጸው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ወላጅ አጥ ሆነው እንዳደጉ በደንብ ይታወቃል፡፡ መደበኛም ሆነ ኢ-መደበኛ ከሆኑ ት/ቤቶች ምንም አልተማሩም፡፡ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች ወይም ከብልሆችም አልተማሩም፡፡ ይልቁንም እርሳቸው ያለ ቀለም ትምህርት ነብይ ናቸው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ያደገው በጥበብ ነበር፡፡

[10] Answering Christianity.com

*ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት፣ በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር፡፡ (ሉቃስ 2፡52)*

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ኢየሱስን (ዐለይሂስ ሰላም) ደንቆሮና ዕውር ብሎ መጥራት የማያስኬድ ነው፡፡ አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ራሱ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ደንቆሮና ዕውር እንዲሆኑ መርጧል፡፡ እንዲሁም ከመወለዳቸው በፊት የርሳቸውን ባህሪያት በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሷል፡፡

*ከእርሱ በፊትም መጽሐፍን የምታነብ በቀኝህም የምትጽፈው አልነበርክም፡፡ ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በርግጥ በተጠራጠሩ ነበር፡፡ (አል-ቁርኣን 29፡48)*

9. *(ኢሳይያስ 42፡20-22)* የመጨረሻው ነገር ግን ዝቅተኛ ያልሆነው የማብራሪያ ነጥብ የአምላክ ሕግ ታላቅነት ሲረጋገጥ የአምላክ ባሪያ *በኢሳይያስ 42፡20-22* በተጠቀሰው መሠረት የተላከ ጊዜ ነበር፡፡

*ብዙ ነገርን ታያላችሁ ነገር ግን አትጠባበቁም፤ ጆሮአችሁም ተከፍተዋል ነገር ግን አትሰሙም፡፡ እግዚአብሔር ስለጽድቁ ሕጉን ታላቅ ያደርግና ያከብር ዘንድ ወደደ፡፡*

*(ኢሳይያስ 42፡20-22)*

በዚያ ውስጥ ለነርሱ ወስነናል፡-

*ከውስጧም፡- "ነፍስን በነፍስ፣ ዓይንን በዓይን፣ አፍንጫን በአፍንጫ፣ ጆሮን በጆሮ፣ ጥርስን በጥርስ፣ ቁስሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ" የሚል ድንጋጌ አሰፈርንላቸው፡፡ (በደሉን) ይቅር ያለ (ተበዳይ) ይህ ድርጊቱ ኃጢአቱን ያሰርይለታል፡፡ አላህ ባወረደው ያልፈረዱ እነርሱ በርግጥም በዳዮች ናቸው፡፡ (አል-ቁርኣን 5፡45)*

ተመሳሳይ ነገር በብሉይ ኪዳን ያለ ምንም ፊደል ልዩነት ይገኛል፡፡

***ዓይንህም አትራራለት፤ ነፍስ በነፍስ፣ ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር ይመለሳል፡፡ (ዘዳግም 19፡21)***

የኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ጠበቆች ያ ቃል የተገባው ሕግ ተሰርዟል በማለት ያስተምሩናል፡፡ ያ ደግሞ የኢሳይያስ 42 መሲሓዊ ትንቢትን ሐሰት ያደርጋል፡፡ የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አስተምህሮ የአምላክን ሕግ የዘላለም አስፈላጊነቱን አረጋግጧል፡፡ ይህም የትንቢቱን በርሳቸው መፈጸም ያመለክታል፡፡

***ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፣ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትዕዛዝ ተሽራለች፣ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል፡፡***

***(ዕብራውያን 7፡18-19)***

## የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል

ውድ አንባቢያን! ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የተነገሩ ትንቢቶችን አስመልክቶ የተወሰኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን ከብሉይ ኪዳን ለመመርመር ችለናል፡፡ አሁን ደግሞ ከአዲሱ ኪዳን ውስጥ ለመፈለግ እንሞክራለን፡፡

***የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፣ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፣ የሚመጣውንም ይነግራችኋል፡፡ እርሱ ያከብረኛል፣ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና፡፡ (ዮሐንስ 16፡12-14)***

የክርስቲያኖች የዚህ ትንቢት ትርጉም ለመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እኛ በሚገባ ለምደናል፡፡ ግና መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) የጥምቀት ወቅት ቀድሞ ወርዷል፡፡

***ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃው ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ (ማቴዎስ 3፡16)***

*በዮሐንስ 16፡12-14 "እርሱ"* የሚለው የሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር *መንፈስ ቅዱስን አያመለክትም፣* ይልቁንም ከኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) በኋላ *የሚመጣ* የሆነውን የሰውን ልጅ *ያመለክታል፡፡*

ጥሩ ማስረጃ *ያ የዚህን ትንቢት ለመንፈስ ቅዱስ መተርጎምን መና የሚያስቀረው ይህ እንዲህ የሚለው ዐ.ነገር ነው፡-*

***"የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፡፡"***

በክርስትና *ሥላሴ* የሦስት እኩል የሆኑ ጌቶች ውህደት *እንደመሆኑ መጠን፡ ማለትም - አባት፣ ልጅና መንፈስ ቅዱስ -* በአንድነትና በስምምነት በዓለም ላይ እኩል *ሥልጣን ያላቸው* ስለሆኑ ይህን ትንቢት *ለመንፈስ* ቅዱስ *ለመተርጎም መሞከር* ከንቱ ልፋት *ነው፡፡* ምናልባት ይህ ትንቢት ለሦስተኛው የ*ሥ*ላሴ አካል ይገባል የሚል ክርክር ከመጣ፣ ይህ የሚ*ያመለክተው* ሦስተኛው የ*ሥ*ላሴ አካል - *መንፈስ* ቅዱስ - እርሱ "ከራሱ *መናገር* የማይችል፣ ግና የሰማውን ብቻ የሚናገር" ከሆነ፣ ማለትም እንደዚህ *ሥልጣን* አልባ ጌታ ከሆነ ይህ የ*ሥ*ላሴ አካል የሆነውን የ*መንፈስ* ቅዱስን *ሥልጣን*ና ዕውቀት አዘቅት ውስጥ ይከታል፡፡ እንዲሁም ይህ የሚሆን ከሆነ፣ ይህ *ሥ*ላሴን በ*መደምሰስ* ክርስትናን *መጨረሻ* የሌለው ውድቀት ውስጥ ይከታል፡፡ ለመሆኑ ከማነው የሚሰማው? እርሱ ከአምላክ ይሰማል የሚል *መከራከሪያ* ነጥብ ከተነሳ ይህ የርሱን የ*ሥ*ላሴ አባል አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ነገር ግን ይህ

ትንቢት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መምጣት ተፈጽሟል፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ (ዐለይሂስ ሰላም) ተልዕኮ 600 ዓመታት በኋላ እርሱ ሳይጨርስ የተወውን ለማጠናቀቅ ብቸኛው ነብይ ናቸው፡፡ ከኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) አስተምህሮ ጋር የሚስማማ ከአል-ቁርኣን ጥሩ ማስረጃ አለን፡፡

*"እርሱ ከራሱ ስሜት አይናገርም፡፡" (አል-ቁርኣን 53፡3)*

የመጨረሻው ነብይ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የኢየሱስ ክርስቶስን (ዐለይሂስ ሰላም) ትክክለኛ ማንነት ለዓለም አስተምረዋል፣ እርሱን እንደ ታላቅ የአምላክ ነብይ አክብረዋል፡፡ እንዲሁም ከዚያ አይሁዶች እርሱንና እናቱን የውሸት ክስ ውስጥ ከወረወሩበት ስም ማጥፋት ንጹሕ አድርጎታል፡፡

## ታማኙና እውነተኛው፣ እርሱ ማነው?

ይህም ሌላው በጣም አስፈላጊና ተዛማጅነት ያለው በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰ ትንቢት ነው፡፡ ከዚህ ራዕይ ጀርባ ያለውን ምስጢር ለማውጣት የበለጠ ጥልቅ የምንሄድበት ይሆናል፡፡

***ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፣ እነሆም በአምባ ላይ ፈረስ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፣ በጽድቅም ይፈርዳል፣ ይዋጋልም፡፡ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፣ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፣ ከእርሱ በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተፃፈ ስም አለው፣ በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል፣ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል፡፡ በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምበላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር፡፡***

***(ራዕይ 19፡11-14)***

እንደ ክርስቲያኖች አመለካከት የዚህ ዓይነት ሰው በዚህ ዓለም ታይቷል? ፍርድ ሰጥቷል? ለጦርነቶች ዘመቻዎችን

አድርጓል? እርሱ ብቻ የሚያውቀው ስም ነበረው? እነዚህ በጣም ወሳኝ የሆኑ ፊር ቀዳጅ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ሁሉም መልሶች አዎ! ናቸው፡፡ ለምንና እንዴት አዎ ሆኑ? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ጋር በማዛመድ የራሳችሁን መጽሐፍ ቅዱስ በጥልቅ ማንበብ ለናንተ ይመከራል፡፡ በጥልቅ ማንበብ ማለት ምን እንደሆነ እስቲ ከሚቀጥለው እንይ፡-

"ቀጥሎ ካሉት ነገሮች መካከል አንዱንም ከማለትህ በፊት ምክንያታዊ በሆነ እርግጠኝነት "እኔ ተገንዝቤያለሁ" ማለት መቻል አለብህ፡- "ተስማምቻለሁ" ወይም "አልተስማማሁም" ወይም "ውሳኔዬን አግኝለሁ" ከማለትህ በፊት፡፡ መተቸት ማለት ሁልጊዜ አለመስማማት (እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ተጠራጣሪ መሆን) ነው በሚል ታሳቢነት ስህተት እንደማትፈጽሙ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ያለመታደል ሆኖ ይህ የተለመደ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው፡፡ መስማማት ማለት ልክ እንደ አለመስማማት ሁሉ ባንተ ላይ የወሳኝ ፍርድ ልምምድ ይሆናል፡፡ ያለ ግንዛቤ መስማማት ሞኝነት ነው፡፡ ያለግንዛቤ አለመስማማት ዓይን አውጣነት፡፡"[11]

ቀጥሎ ያሉት የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስብዕናዎች ዕውቀት ፈላጊ በሆነ አዕምሮ ለመመርመር ከተሞከሩ የዚህን ትንቢት ተፈፃሚነት የሚያረጋግጡ ናቸው፡-

1. ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በተለምዶ ታማኙ ወይም ሙሐመድ "አል-አሚን" ተብለው ይጠሩ ነበር፤ ምክንያቱም እርሳቸው በማሕበረሰባቸው ውስጥ የእውነት ሰው በመሆናቸው፡፡ በምድር ላይ ከተራመዱ

[11] መልሶ የመስጠት ሥነ-ምግባራት፣ "መጽሐፍ እንዴት እንደሚነበብ፣ ገጽ 241"

ሰዎች ሁሉ ማንም እንደ ኢስላም ነብይ ታማኝ አልነበረም፣ መሆንም አይችልም፡፡

2. “ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከጦር ግንባር አንዴም ሸሽተው አያውቁም፤ እርግጠኛ ለመሆን የበለጠ መንገር ካስፈለገ እውነታው ሌላው ቀርቶ አላፈገፈጉም፡፡ ጠላት በሚያጠቃበት ጊዜ ሌሎች በመከላከል ጥቂት ወይም የበለጠ እርምጃዎችን ወደኋላ ከሄዱ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንድ ኢንች መሬት እንኳን ለጠላት ለመስጠት ባለመፈለግ ቦታቸውን ጠብቀው ቆይቷል፡፡”[12]
3. ከነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ባልደረቦች አንዱ ሰልማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) የፋርስ ዝርያ የሆነው፣ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በራሳቸው ላይ የተፃፈ ስም እንዳላቸው የተረጋገጠውን እውነታ ሲፈልግ ነበር፡፡

“ሰልማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) በተለያዩ ቋቋሳት ጥገኝነት ተሰጥቶታል፡፡ እናም የመጨረሻ ቋቋሱን ሞት የቀረበው ጊዜ፣ ሰውዬው “አንተ ልጅ ሆይ! እኛ እንደሆንን ትክክለኛ ሃይማኖት ላይ የሆነን አንድም ሰው አላውቅም፡፡ ነገር ግን በሕይወት ዘመንህ ውስጥ ነብይ ይነሳል፣ ይህ ነብይም እንደ አብርሃም (ዐለይሂስ ሰላም) ተመሳሳይ ሃይማኖት ላይ ነው”[13] አለው፡፡ ቋቋሱ በሰልማን ዕድሜ ስለሚመጣው ስለዚህ ነብይ ባህሪ እንደሚከተለው አብራርቷል፡- ስጦታ የተለገሰለትን ምግብ ይቀበላል፣ ይበላልም፣ ምጽዋትን ግን አይቀበልም/አይበላምም፣ እንዲሁም የነብይነት አርማው በትከሻዎቹ መካከል ይሆናል፡፡ ሰልማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ብዙ ፈተናዎችን ካለፈ በኋላ መዲና ደርሶ ነብዩን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ለርሳቸው ምግብ እንደ ስጦታና እንደ ምጽዋት በማቅረብ ፈተናቸው፡፡ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የመጀመሪያውን

[12] ሙሐመድ፣ አንተ እርሱን ልክ ማየት እንደምትችለው፣ ገጽ 106
[13] እውነታን በመፈለግ ሂደት፣ ገጽ 27

የበሉና ሁለተኛውን የተውት ጊዜ ሰልማን በርሳቸው ላይ ስም መፃፍ አለመፃፉን ለማረጋገጥ ሄደ፡፡

ሰልማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዳለው ለርሳቸው ሰላምታ አቀረብኩና ከዚያም ያን ለኔ በባልደረባዬ የተገለጸልኝን (የነብይነት) ማህተሙን ለማየት በመሞከር ወደ ጀርባቸው ሄድኩኝ፡፡ እርሳቸው (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እኔ (ይህን) ሳደርግ ባዩኝ ጊዜ እኔ አንድ ለኔ የተገለጸልኝን ነገር ለማረጋገጥ እየሞከርኩ መሆኔን አወቁ፡፡ ልብሳቸውን ከጀርባቸው ላይ አነሱና እኔም ማህተሙን ተመለከትኩኝ፡፡ ተገነዘብኩትም፡፡ እየሳምኩና እያለቀስኩ እዚያ ላይ ወደቅኩ፡፡"[14]

4. እስቲ የሰማይ ሠራዊቶች ነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዴት እንደተከተሉት ቀጥሎ ካለው የአል-ቁርኣን አንቀጽ እናንብብ፡-

***"ጌታህም ለመላእክት "እኔ ከናንተ ጋር ነኝ፡፡ አማኞችን አጠናክሩ፡፡ በነዚያ በካዱት ሰዎች ልቦች ውስጥ ፍርሃትን እለቃለሁ፡፡ አንገቶቻቸውን ምቱ፡፡ ጣቶችን ሁሉ ምቱም፡፡" የሚል መልዕክት ባስተላለፈ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡፡"***

***(አል-ቁርኣን 8፡12)***

እስቲ አንድ ተጨማሪ ነጥብ ከሐዲሥ ደጋፊ ማስረጃ የሆነን እንጨምርና ከዚያም የራሳችሁን ውሳኔ ትወስዱ ዘንድ ለናንተ እንተወው፡፡

እብን ዐብ-ባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- "በርግጥ፣ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የበድር ቀን እንዲህ ብለዋል፡- ይህ

[14] እውነታን በመፈለግ ሂደት፣ ገጽ 27

ጂብሪል ነው የፈረሶቹን ልጓም የያዘ፣ እንዲሁም በርሱ ላይ የጦር መሣሪያ ነው፡፡"[15]

*ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፣ እነሆም በአምባ ላይ ፈረስ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፣ በጽድቅም ይፈርዳል፣ ይዋጋልም፡፡ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፣ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፣ ከእርሱ በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተፃፈ ስም አለው፣ በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል፣ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል፡፡ በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምበላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር፡፡*

*(ራዕይ 19፡11-14)*

አስተያየት፡- ለመሆኑ ክርስትና ፖለቲካዊ ወይስ መንፈሳዊ ሃይማኖት ነው? መንፈሳዊ ከሆነ የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ መጽሐፍ ስሙ ሙሐመድ "አል-አሚን" ወይም ታማኙ የሚባል ሰው እንደሚመጣ አስቀድሞ በትንቢት ተናግሯል፡፡ እርሱም የመጣ ሲሆን በሰዎች መካከል ፍርድ ሰጥቷል፣ የንጉሶች ንጉስ ሆኗል፣ የሰማይ ሠራዊት ከርሱ ጋር የተዋጉበትን ጦርነት መርቷል፣ እንደዚሁም በራሱ ላይ የተፃፈ ስም ነበረው፣ ያ እርሱ ብቻ የሚያውቀው የሆነው፡፡ አሁን የሃይማኖታዊ ፍላጎት እጥፋት ከክርስትና ወደኢስላም መዞር አለበት፤ ክርስትናን መከተል ለፖለቲካዊ ወይም ለኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች እስካልተፈለገ ድረስ፡፡ ኢስላም ሌላ ነገር አይደለም ግና የነዚያ ብዙ ነገሮች ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ማለት የሚገባቸው ቀጣይ ሲሆን የነብያት ሁሉ መደምደሚያ በሆኑት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል፡፡

---

[15] ሰሒሕ አል-ቡኻሪ፣ የጦርነት መጽሐፍት፣ ምዕራፍ "የመላእክት በበድር መገኘት" ሐዲሥ ቁጥር 3995

*ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ መካከል የአንዱም አባት አይደለም፡፡ ግና (እርሱ) የአላህ መልዕክተኛና የነብያት መቋጫ ነው፡፡ አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ ነውና፡፡ (አል-ቁርኣን 33፡40)*

5. *"በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፣ ከእርሱ በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተፃፈ ስም አለው፣ በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል"* የሚሉት ከኢስላማዊ ኢ.ማማና አልባሳት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡

*"ከነርሱ ጋር ያለውን (መልዕክት/ተውራትን) አረጋጋጭ የሆነ መልዕክተኛ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ፣ ከነዚያ መጽሐፉን ከተሰጡት ከፊሎቹ የአላህን መጽሐፍ (ተውራትን) ምንም ነገር እንደማያውቁ ሆነው ወደኋላቸው ወረወሩት፡፡" (አል-ቁርኣን 2፡101)*

## መካን (በካን) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታውቃታላችሁ?

መካ ሌላ ስሟ በካ ነው፡፡ "በካ" ማለት ደግሞ ልቅሶ ማለት ነው፡፡ ሙስሊሞችን ለማሳፈር በክርስቲያኖች በተደጋጋሚ የሚጠየቀው በጣም ፈታኙ ጥያቄ ስለሙስሊሞች የሶላት አቅጣጫ ነው፡፡ እነዚያ የዚህን ዓይነት ጥያቄ የሚጠይቁ በአል-ቁርኣን ውስጥ በአላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ቂሎች ተብለው ተጠርተዋል፡፡

*ከሰዎች መካከል ቂሎቹ፡- "ከዚያ ከነበሩበት ቂብላ ምን አዞራቸው?" ይላሉ፡፡"ምስራቁም፣ ምዕራቡም የአላህ ነው፣ የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል" በላቸው፡፡*

*(አል-ቁርኣን 2፡142)*

ሙስሊሞች በሶላት ወቅት ወደ ካዕባ አቅጣጫ እንዲዞሩ በአላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ታዘዋል፡-

*የትኛውም (ሕዝብ) የስግደት አቅጣጫ (ቂብላ) አለው፤ ወደ መልካም ሥራዎች ተሽቀዳደሙ፡፡ የትም ብትሆኑ አላህ ይሰበስባችኋል፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና፡፡*

*(አል-ቁርኣን 2፡148)*

*ከየትም (ለጉዞ) ከወጣህበት ሥፍራ ሆነህ (በስግደት ወቅት) ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ አቅጣጫ አዙር፡፡ እርሱ በርግጥም ከጌታህ የተላለፈ እውነት ነው፡፡ አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዘንጊ አይደለም፡፡ (አል-ቁርኣን 2፡149)*

ስለሙስሊሞች የሶላት አቅጣጫና ከዚህ ጋር የተያያዘውን የክርስቲያኖችን ትችት በምናይበት ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስን (ዐለይሂስ ሰላም) ትንቢት፣ ወደፊት ከርሱ በኋላ፣ ያ የሶላት አቅጣጫ መቀየርን ምልክት ለማሳየት የተነገረውን ማየት አለብን፡፡

*ሴቲቱ፡- ጌታ ሆይ፣ አንተ ነብይ እንደ ሆንህ አያለሁ፡፡ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፣እናንተም፡- ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አላት፡- አንቺ ሴት፣ እመኚኝ፣ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፡፡ (ዮሐንስ 4፡19-21)*

ይህ የሆነበት ምክንያት ወደፊት አምላክ በዚያ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ውስጥ የማይመለክበት ግና በመካ የሚመለክበት ጊዜ የሚመጣ ሲሆን ሙስሊሞች በአምልኮአቸው ወቅት ወደ ካዕባ የዞሩበት ከዚህ እውነታ የተነሳ ነው፡፡ ከዚህ ሐሳብ ጋር የሚስማማ ቁርኣናዊ ማስረጃ አለን፡፡

*ለሰው ልጅ የተቀመጠው የመጀመሪያው (የአምልኮ) ቤት ያ በበካ የሚገኘው ነው፡፡ የተባረከና ለዓለማትም መመሪያ (የሚፈልቅበት) እንዲሆን ተደረገ፡፡ ከውስጡ ግልጽ ተዓምራት ይገኛሉ፡፡ (ከነኝህ መካከል) የኢብራሂም መቆሚያ (አንዱ ነው)፡፡*

*ከርሱ ውስጥ የገባ ሰላምን ይጎናጸፋል፡፡ ቤቱን - ወደርሱ መጓዝ ለሚችሉ ሁሉ - ይጎበኙ ዘንድ አላህ በሰዎች ላይ ግዴታ አድርጓል፡፡ ግና ያስተባበለ (ከራሱ ውጭ ማንንም አይጎዳም)፡፡ አላህ ከዓለማት የተብቃቃ ነው፡፡ (አል-ቁርኣን 3፡96-97)*

መጽሐፍ ቅዱስ በበካ (በልቅሶ) ሸለቆ ውስጥ ስለሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቶችም ይጠቅሳል፣ መዝሙረ ዳዊት 84፡6 ሐጅና የዘምዘም ውኃን አስመልክቶ የሚናገረው አለ፡፡

*በልቅሶ ሸለቆ ውስጥ በወሰነው ስፍራ የህግ መምህር በረከትን ይሰጣልና፡፡ (መዝሙረ ዳዊት 84፡6)*

*"እነርሱ የበካ ሸለቆ ውስጥ ሲያልፉ፣ የምንጮች ስፍራ አደረጓት፤ የመከር ዝናቦችም በኩሬዎች ይሸፍኗታል፡፡" (መዝሙረ ዳዊት 84፡6፣ ከኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን የተወሰደ)*

*"በልቅሶ ሸለቆ አጠገብ አለፉ፤ የመኖሪያ ስፍራም አደረጓት፤ እንደዚሁም የህግ መምህርን በረከት ይሸፍነዋል፡፡" (መዝሙረ ዳዊት 84፡6 የአረማይክ መጽሐፍ ቅዱስ፣ በቀላል እንግሊዘኛ ከሚለው የተወሰደ)*

ውድ ክርስቲያኖች! የሕግ አስተማሪው፣ ያ በበካ ወይም በልቅሶ ሸለቆ በበረከት ሊሸፈን የተነገረለት ማነው? እርሱ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነው፡፡

## መካ ወይስ ጽዮን? (ኢሳይያስ 60፡1-22)

ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት ለመካ ሳይሆን ለጽዮን የተነገረ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ግና ለዚህ ትንቢት ስለመካ ከሙስሊሞች ይገባናል በቂ ማስረጃ አንፃር የፈለጉትን የጋለ ክርክር ቢያደርጉ በተጨባጭ ማስረጃ ፈጽሞ ማረጋገጥ አይችሉም፣ ቀጥሎ ባሉ ነጥቦች ሳቢያ፡-

*አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ፣ ነገስታትም ወደመውጫ ጸዳልሽ ይመጣሉ፡፡ (ኢሳይያስ 60፡3)*

*መፃተኞች ቅጥርሽን ይሠራሉ፣ ነጋሥታቶቻቸውም ያገለግሉሻል፡፡ በሮችሽም ሁልጊዜ ይከፈታሉ፡፡*

*(ኢሳይያስ 60፡10-11)*

1. ሁለቱን ቅዱሳን መስጂዶች - አል-መስጂድ አል-ሐራም በመካ እና አል-መስጂድ አን-ነበዊ በመዲና - የመጠበቅ ኃላፊነት በሳዑዲ ዐረቢያ ንጉስ እንደተወሰደ ዛሬ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ይህ ኃላፊነት በተለምዶ የኸሊፋ ነበር፡፡ ማዕረጉን ለመውሰድ የመጀመሪያው በ1986 የሳዑዲ ንጉስ ፈህድ ብን ዐብዱል ዐዚዝ ነበር፡፡ ንጉስ ፈህድ "ክብርነትዎ" የሚለውን መጠሪያ ወደ "የሁለቱ ቅዱሳን መስጂዶች ጠባቂ" ቀይረዋል፡፡ ተተኪው ንጉስ፣ ዐብደሏህ ብን ዐብዱል ዐዚዝ፣ ከንጉስ ፈህድ ህልፈት በኋላ ተመሳሳይ ማዕረግ በ2005 ወስደዋል፣ የግማሽ ወንድሙን፡፡ *"ነጋሥቶቻቸውም ያገለግሉሻል"* የሚለውና "*ኻድማል ሐረመይን"* ትንቢቱን በመካ መፈጸሙን ከማሳየትም በላይ አንዱ የሌላው ነጸብራቅ ነው፡፡ የሳዑዲ ዐረቢያ ንጎሶች የነርሱ የቅዱሳን ስፍራ ጠባቂነት በመጽሐፍ ቅዱስ ከኢየሱስና ከሙሐመድ (በሁለቱም ላይ የአላህ ሰላምና በረከት ይሁንና) መወለድ ረጅም ዓመታት አስቀድሞ ሲነገርላቸው እንዴት የታደሉ ናቸው፡፡

ሮማውያን ታላቁን የአይሁዶች አመጽ፣ ያን ከአራት ዓመት በፊት አስቀድሞ የተጀመረውን መቶ በመቶ ከፍፃሜ ለማድረስ ኢየሩሳሌምና መቅደሱን በ70 ዓ.ዓ በቲተስ ዘመን አፍርሰዋል፡፡

*ስለዚህ በእናንተ ምክንያት ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች፣ ኢየሩሳሌምም የድንጋይ ክምር ትሆናለች፣ የቤቱም ተራራ እንደ ዱር ከፍታ ይሆናል፡፡ (ሚክያስ 3፡12)*

*የእግዚአብሔርን ቤትና የንጉሱን ቤት አቃጠለ፣ የኢየሩሳሌምንም ቤቶች ሁሉ፣ ታላላቆችን ቤቶች ሁሉ በእሳት አቃጠለ፡፡ (ኤርምያስ 52፡13)*

(እንዲሁም "የአይሁዶች ሦስት ሳምንት ሐዘን" ይመልከቱ)

ይህ ትንቢት በጽዮን ውስጥ እውን ሆኗል ብለው ለመተርጎም መሞከር መሳለቅ ነው፤ ምክንያቱም ከታሪክ መሸሽ አንችልምና፡፡ ያለፈውና ያሁኑ የጽዮን ታሪክ፣ ያ እኛ በተግባር የምናውቀው ይህን እንዲህ የሚለውን ትንቢት ይቃረናል፡-

*አለቆችሽንም ሰላም፣ የበላይ ገዢዎችሽንም ጽድቅ አደርጋለሁ፡፡ (ኢሳይያስ 60፡18)*

ባሁን ወቅት ቴሌቪዥን የሚመለከቱ ወይም ራዲዮ የሚያዳምጡ ከሆነ ይህን መጽሐፍ እያነበቡ እያሉ እንኳን እንደው እርስዎ ከወደ ጽዮን የሰላም ወይስ የጦርነት ድምጽ እያለሁ ወይም እሰማለሁ ብለው ያስባሉ? የጽዮንን የድሮና ያሁን ሁኔታ ከዚህ ትንቢት ጋር የምናስተያይ ከሆነ እውነታው ገሃድ ይሆናል፡፡ የጽዮንን ብጥብጥ በአዕምሮአችን ውስጥ በመያዝ መካ ሰላምን፣ ፀጥታና መረጋጋትን የምታሟላ ሆና ሳለች ይህን ትንቢት ለጽዮን መተርጎም የተሳሳተ ግንዛቤ ወይም መሃይምነት ነው፡፡ ቀጥሎ ካለው ጥቅስ አንፃርም መካ ለትንቢቱ ተገቢ ናት፡-

*ከዚያ በኋላ በምድርሽ ውስጥ ግፍ፣ በዳርቻሽም ውስጥ ጉስቁልናና ቅጥቃጤ አይሰማም፡፡ (ኢሳይያስ 60፡18)*

2. የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ መጽሐፍ ስለቅዱስ ስፍራ ሰላማዊነት፣ ፀጥታ፣ መረጋጋት፣ እና ሀብታምነት፣ ያ የዓለም ብልጽግና ሁሉ ወደርሷ ስለሚመጣው በትንቢት ተናግሯል፡፡ ለመሆኑ ይህች ከተማ ጽዮን ናት?

***በዚያን ጊዜ የባሕሩ በረከት ወደ አንቺ ስለሚመለስ፣ የአሕዛብም ብልጽግና ወደ አንቺ ስለሚመጣ አይተሽ ደስ ይልሻል፡፡ (ኢሳይያስ 60፡5)***

እንደ መታደል ሆኖ፣ በዓለም ላይ መካ ብቸኛዋ ቅዱስ ከተማ ናት፣ እነዚያን ከላይ የተገለጹትን ባህሪያት በሚገባ የምታሟላ - ብታምኑም ባታምኑም፡፡

ዛሬ ዛሬ፣ መካን በየዓመቱ ከ13 ሚሊዮን በላይ ሙስሊሞች ይጎበኟታል፣ በሐጅ ጥቂት ቀናት ውስጥ በየዓመቱ ለዑምራም በርካታ ሚሊዮን ጎብኚዎችን ጨምሮ፡፡ ከዚህ የተነሳም መካ በሙስሊሙ ዓለም በጣም ዓለም አቀፋዊና የተለያዩ ሕዝቦች ከሚገኙባቸው ከተሞች አንዷ ሆናለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዓለም ላይ ያሉትን ሙስሊሞች፣ ደሃና ሀብታም ሙስሊሞችን፣ እነዚያን ወደዚህች ቅድስት ስፍራ ለመሄድ የገንዘብ አቅም ያላቸውን አንድ ታደርጋለች፡፡ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ቅድስት ስፍራ በመሆን ቆይታለች፡፡ እስቲ አል-ቁርአን ስለመካ ደህንነት የሚለውን እንመልከት፡-

***ኢብራሂምም፡- "ይህንን ሀገር ሰላም የሰፈነበት፣ ፀጥታ የነገሰበት አድርግ፡፡ ከነዋሪዎቹም በአላህ እና በመጨረሻው ቀን ላመኑት ከፍራፍሬዎች ሲሳይ ለግስ" ባለ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡፡ (አላህም)፡- "(ሲሳይን ለአማኞች እንደሚለግስ ሁሉ) ለዚያ ለካደውም (እለግሰዋለሁ)፡፡ (በዚህች ዓለም) ጥቂት አጣቅመዋለሁ፡፡ ከዚያም (በመጭው ዓለም) ለእሳት ቅጣት እዳርገዋለሁ፡፡ (እሳት) እጅግ አስከፊ መመለሻ ናት" አለ፡፡***

***(አል-ቁርኣን 2፡126)***

*(ኢብራሂምም አለ) "ጌታችን ሆይ! እኔ አዝመራ በሌለው ሸለቆ ውስጥ በተከበረው ቤት (ካዕባ) አጠገብ ከዘሮቼ አስቀመጥኩ፡፡ ጌታችን ሆይ! ሶላትን ያቋቁሙ ዘንድ (አስቀመጥኳቸው)፡፡ ከሰዎችም ልቦችን ወደእነሱ የሚናፍቁ አድርግ፡፡ ያመሰግኑህም ዘንድ ከፍሬዎች ስጣቸው፡፡" (አል-ቁርኣን 14፡37)*

*የቁረይሾች ልምድ (አላህ የለገሳቸው ፀጋና ያደረገላቸው ጥበቃ መገለጫ ነው)፡፡ (አላህ በዚህ ጥበቃና እንክብካቤ) በበልግ (ወደየመን)፣ በበጋ ደግሞ (ወደ ሻም) የሚያደርጉትን ጉዞ እንዲላመዱት (ያለ ምንም ፍርሃት በሰላም እንዲፈጽሙት) አደረጋቸው፡፡ (በነዚህ ጉዳዮች አማካኝነት ላገኟቸው ፀጋዎች ውለታ ምላሽ) የዚህን ቤት (የካዕባን) ጌታ ያምልኩ፡፡ ያንን ከረሃብ የመገባቸውን፣ ከፍርሃትም ነፃ (አውጥቶ) ሰላምን ያጎናጸፋቸውን (ጌታ ያምልኩ)፡፡ (አል-ቁርኣን 106፡1-4)*

*የግመሎች ብዛት፣ የምድያምና የጌፌር ግመሎች ይሸፍኑሻል፤ ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፣ ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ፣ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ፡፡ (ኢሳይያስ 60፡6)*

የዚህን ትንቢት በጽዮን መፈጸም ውድቅ ማድረግ እንችላለን፤ ምክንያቱም ሳባ የምትገኘው በየመን ውስጥ ነው፡፡ ከየመን፣ የሙስሊም ሀገር ከሆነች፣ የግመሎች መንጋ የመካን ምድር ሸፍኖ በተግባር እየታየ ሳለ እንዴት ነው የምትፈርደው? እንደ ሳባ ካሉ ከሙስሊም ሀገሮች የግመሎች ብዛት መሸፈን ወደ ጽዮን መቼም አልተከሰተም፣ ወደፊትም አይከሰትም፡፡

*የቄዳር መንጋዎች ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባሉ፣ የነባዮትም አውራ በጎች ያገለግሉሻል፣ እኔን ደስ ሊያሰኙ በመሠዊያዬ ላይ ይወጣሉ፣ የክብሬንም ቤት አከብራለሁ፡፡ (ኢሳይያስ 60፡7)*

ነባዮትና ቄዳር የበኩርና የሁለተኛው የእስማዔል (ዐለይሂስ ሰላም) ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው፡፡ የነርሱ መንጋዎችና አውራ

በጎች መካን እያገለገሉ ናቸው፡፡ ይህ ትንቢት በዐረፋ ቀን የሚደረጉትን የእርድ ሥነ-ሥርዓቶች የሚነግረን መሆኑን ያመለክታል፡፡ አመክንዮ (ሎጂክ) አንድን የክርክር ነጥብ ወይም ምክንያታዊ መረጃን እንድታስተነትንና ከዐረብ መሬት የሆኑ መንጋዎችና አውራ በጎች ጽዮንን ወይስ መካን እያገለገሉ ስለመሆናቸው እንድትደርስበት ያደርገሃል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሞት የተከሰተው እንደ የመጨረሻው የኃጢአት ማስተሰሪያ እንደሆነ ታምናለች፡፡ እናም ያን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን የእርድ አስፈላጊነት ከንቱ አድርጎታል፡፡ በኢስላም እንስሳትን መሰዋት ዓመታዊ የተለመደ ተግባር ነው፡፡

*ከሰውም ማንም እስከማያልፍብሽ ድረስ የተተውሽና የተጠላሽ ነበርሽ፤ ነገር ግን የዘላለም ትምክህትና የልጅ ልጅ ደስታ አደርግሻለሁ፡፡ (ኢሳይያስ 60፡15)*

ጽዮን የተተወች አልነበረች፤ ምክንያቱም እርሷ ከታሪክ መነሻ ጀምሮ ፖለቲካዊ፣ ቅኝ አገዛዛዊ እና መንፈሳዊ ማዕከል ነበረች፡ ግና መካ እንዲህ አልነበረችም፡፡ መካ ዓለም ዓቀፋዊ ከተማ የሆነችው ከኢስላም በኋላ ነው ማለትም ከዚህ ትንቢት መፈጸም በኋላ፡፡ እንደዚሁም እርሷ ወደፊትም ለሁሉም ትውልድ የደስታ ቦታ ናት፡፡

## ቂብላ በመጽሐፍ ቅዱስና በአል-ቁርኣን

ቂብላ የሚለው ቃል በአል-ቁርኣን ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው *(አል-ቁርኣን 10፡87)* በተገለጸው መሠረት የሶላት አቅጣጫን ለመጠቆም ነው፡፡ እንዲሁም የበለጠ አጠቃላይ በሆነ መንፈስ ለሐጅ የትኩረት አቅጣጫችን ነው፡፡ ከአል-ቁርኣን 2፡143 እንደምናነበው አምላክ ቂብላን ለውጧል፣ እንደዚሁም በዚህ ለውጥ ውስጥ ለመልዕክተኛው ተከታዮች በውስጡ ፈተና አለው፡፡

***(ሙሐመድ ሆይ!) አንተ የነበርክባትን ቂብላ ለሌላ (ነገር) አላደረግንም (ከካዕባ ወደ ቤይተል መቅዲስ እንድትዞር ያዘዝንህ) መልዕክተኛውን የሚከተለውን ወደ ክህደት ከሚመለሰው ለይተን ለማወቅ እንጂ፡፡ (አል-ቁርኣን 2፡143)***

*"አንተ የነበርክባትን ቂብላ ለሌላ (ነገር) አላደረግንም"* የሚሉት ቃላት አምላክ ቂብላ መቀየሩን ያረጋግጣሉ፡፡ *"አንተ የነበርክባትን"* በሚሉት ቃላት ውስጥ የአላፊ ግስ አጠቃቀምን ያስተውሉ፡፡ አል-ቁርኣን ስለዚህ ጉዳይ በሚቀጥሉት ቃላት ሙሉ ማብራሪያ ይሰጣል፡-

***ከየትም (ለጉዞ) ከወጣህበት ሥፍራ ሆነህ (በስግደት ወቅት) ፊትህን ወደ ተከበረው መስጂድ አቅጣጫ አዙር፡፡ እርሱ በርግጥም ከጌታህ የተላለፈ እውነት ነው፡፡ አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዘንጊ አይደለም፡፡ (አል-ቁርኣን 2፡149)***

ከላይ ያሉት ቃላት በአምላክ ለአማኞች የተቀመጠው ፈተና የተያያዘው ማን አዲሱን ቂብላ (መስጂድ አል-ሐራም) እንደሚከተልና ማን መልዕክተኛውን እንደሚያምጽና በአሮጌው ቂብላ ላይ እንደሚቆይ ያረጋግጣሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ወሳኝ እውነታም ከሌሎች አንቀጾች እናገኛለን፡፡ አል-ቁርኣን በራዕይ ከመገለጹ በፊት፣ እንደዚሁም ምናልባትም በራዕዩ የመጀመሪያ ዓመታት፣ በርግጥ በርካታ ቂብላዎች እንደነበሩ አል-ቁርኣን ይጠቁማል፡፡ ምክንያቱም (በአል-ቁርኣን 10፡87 *መሠረት*) አምላክ የበፊተኞቹን ቂብላዎች ለሌሎች ሕዝቦች ማድረጉን ስለምናውቅ እነዚያ ተግባር ላይ ካሉት ቂብላዎች የተወሰኑት በአምላክ የተደረጉ ነበሩ ማለት እንችላለን፣ ግና የተወሰኑት ምናልባትም ሰው-ሠራሽ የመሆናቸው ዕድል እንዳለ መቀበል አለብን፡፡ ዋናው ቁም ነገር፣ ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተመለከተው እያንዳንዱ ሕዝብ የራሱ ቂብላ እንደነበረው ቁርኣን

ይነግረናል ፡፡ ከዚህ የተነሳ በመጀመሪያው ዓመታት፣ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሶላት እንዲሰግዱ ትዕዛዝን የተቀበሉ ጊዜ የትኛውን ቂብላ መከተል እንዳለባቸው እርግጠኛ አልነበሩም፡፡

1. *(ሙሐመድ ሆይ!) ለነዚያ መጽሐፉን ለተሰጡት ሕዝቦች እውነተኛነትህን እንዲቀበሉ ማስረጃዎችን ሁሉ ብታቀርብላቸው ቂብላህን ፈጽሞ አይከተሉም፡፡ አንተም ቂብላቸውን ተከታይ አይደለህም፡፡ ከነርሱም ከፊሎቹ የከፊሎቹን ቂብላ ተከታይ አይደለም፡፡ እውነቱ ከደረሰህ በኋላ (ከንቱ) ዝንባሌያቸውን ብትከተል አንተ ያንጊ ከበዳዮች ነህ፡፡ (አል-ቁርኣን 2፡145)*

ይህ አንቀጽ በነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ጊዜ ከአንድ በላይ ቂብላዎች እንደነበሩ ያረጋግጣል፡፡ እንደዚሁም የተለያዩ የመጽሐፉ ሰዎችም የየራሳቸው ቂብላ ነበራቸው፡፡ ይህ ቀጥሎ ካሉት ቃላት ግልጽ ነው፡-

*"ከፊሎቹ የከፊሎቹ ቂብላ ተከታይ አልነበሩም" (2፡145)*

2. *የትኛውም (ሕዝብ) የስግደት (ወቅት ፊቱን የሚያዞርበት) አቅጣጫ - ቂብላ - አለው፡፡* (አል-ቁርኣን 2፡148)

ይህ አንቀጽ እንደገና ከአንድ ቂብላ በላይ እንደነበር ያረጋግጣል፡፡

3. *ለሙሳና ለወንድሙም፡- "ለወገኖቻችሁ (ለተወሰነ ጊዜ) ግብጽ ውስጥ ቤቶችን ሥሩ፡፡ ቤቶቻችሁን ወደቂብላ (አቅጣጫ) አድርጉትም፡፡ ሶላትንም ስገዱ፡፡ ለአማኞችም ብስራትን ንገር" የሚል መልዕክት በራዕይ ገለጽንላቸው፡፡ (አል-ቁርኣን 10፡87)*

በዚህ አንቀጽ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል "ቂብላ" መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ *"ቤቶቻችሁን ወደ ቂብላ አዙሩት"* የሚሉት ቃላት *"ሶላትንም ስገዱ"* የሚለውን ትዕዛዝ አስከትለዋል፡፡ ይህ የሚነግረን ቂብላ የሚለው ቃል በሶላት ወቅት የሚዞርበት የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን ነው፡፡

> ***4. የፊትህን ወደ ሰማይ መገላመጥ (በቂብላ ፍለጋ እይታህን ወደላይ ማንጋጠጥ) እናያለን፡፡ ወደምትወዳት ቂብላ እናዞርሃለን፡፡ ፊትህን ወደተከበረው መስጂድ (መስጂድ አል-ሐራም) አዙር፡፡ የትም ቦታ ሆናችሁ ፊታችሁን ወደርሱ አቅጣጫ አዙሩ፡፡ እነዚያ መጽሐፉን የተሰጡ ወገኖች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) እርሱ (የቂብላው ለውጥ) ከአላህ የሆነ እውነት መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ አላህ ከሚሠሩት ዘንጊ አይደለም፡፡***
>
> ***(አል-ቁርኣን 2፡144)***

ይህ አንቀጽ ለአንድ ሰው፣ ያ እርሱ ወደየትኛው ቂብላ መዞር እንዳለበት አዕምሮውን ማዘጋጀት ለማይችል ምልክት ይሰጣል፡፡ እርግጠኛ ያለመሆኑ የሚያመለክተው (የቂብላዎቹ) ምርጫ በርካታ መሆናቸውን ነው፡፡ አንድ ቂብላ ብቻ ከነበረ ጥርጣሬው አይኖርም ነበር፡፡ እንደዚሁም አንቀጹ ጥርጣሬው የራስን አካባቢያዊ አቅጣጫ ከመመስረት ችግር ይልቅ  የሌሎችን ሕዝቦች ቂብላ ላለመከተል የበለጠ እምቢተኛ መሆንን ይጠቁማል፡፡ ይህ *"(አሁን) ወደምትወዳት ቂብላ እናዞርሃለን"* በሚሉት ቃላት ተረጋግጧል፡፡ *"አንተ ወደምትወዳት"* የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከዚያ ቀደም ሲል ለነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንድ የማያስደስት ነገር እንደነበረ ነው፡፡ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ያኔ እውነተኛ ሃይማኖትን ከአምላክ በሆነው መመሪያ እየተከተሉ ከመሆናቸው እውነታ አንፃር ሲታይ፣ ከዚያ ከጠላቶቻቸው የተበላሸ የጣዖት አምልኮ በተቃራኒ፣ ከነርሱ ተግባራትም፣ ከነዚህም መካከል አንዱ

የነርሱን ቂብላ ሲሆን፣ ራሳቸውን ከነዚህ ሁሉ ለማግለል የፈለጉ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

የክስተቶቹ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይጠቃለላል፡-

1. በአል-ቁርኣን የመጀመሪያዎቹ ጊዜያትና በራዕዩ የቀደምት ዓመታት በርካታ ቂብላዎች ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ ሕዝብ የራሱ ቂብላ ነበረው፡፡ የተወሰኑት ምናልባትም በአምላክ የተደረጉ ነበሩ፣ ግና ከነዚህ ቂብላዎች መካከል የተወሰኑት ሰው-ሠራሽ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከግምት ውስጥ አለማስገባት አንችልም፡፡

2. ራዕዩ ለሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በሚወርድበት ወቅት አምላክ ቂብላው ወደ መስጂድ አል-ሐራም እንዲሆን አድርጎታል፡፡

3. የቂብላ መቀየር በአምላክ ለአማኞች የተቀመጠውን ፈተና ያሳያል፣ ያም ማን መልዕክተኛውን እንደሚታዘዝና አዲሱን ቂብላ እንደሚከተልና ብሎም ማን በአሮጌው ቂብላ ላይ ችክ እንደሚል ይለያል፡፡

## ለቂብላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

ለቅድመ ቁርኣን ቂብላዎች የተጠቀሱ ቁርኣናዊ ማስረጃዎች እነዚያ ስግደት ወደ ተወሰኑ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚደረጉ ከሚናገሩ ከብሉይ ኪዳን ጥቅሶች አንፃር ሊረጋገጡ ይችላሉ፡፡

1. *በዳንኤል 6፡10* ሦስት ዕለታዊ ስግደትን ስለሚፈጽመው ዳንኤል (ወደ እስራኤል መልዕክተኛ ሲሆን) እናነባለን፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ በዞረበት የርሱ ስግደቶች እንዴት እንደተደረጉ እናነባለን፡፡

*ዳንኤል ጽሕፈቱ እንደተፃፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ፣ የእልፍኙም መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንፃር ተከፍተው ነበር፤ ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ፤ አመሰገነም፡፡ (ዳንኤል 6፡10)*

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው እንደሚያሳየው ይሄ አምልኮ (የቂብላ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ መሆን) በሰለሞንና በአባቱ በዳዊት ጊዜ የተጀመረ ነበር፡፡

2. *በነገሥት ቀዳማዊ* ውስጥ ሰለሞንና ሕዝቦቹ እርሱ በኢየሩሳሌም ለአምላክ ወደ ሠራው ቤት እንዴት በቤቱ አቅጣጫ እንደሰገዱ ከ(*ነገሥት ቀዳማዊ* 8፡22-44) እናነባለን፡፡ በነዚህ አንቀጾች ሰለሞን የአምላክ አገልጋዮች፣ የእስራኤል ሕዝቦችና አሕዛብ እርሱ (አምላክ) ወደመረጠው ከተማ (ኢየሩሳሌም)፣ እንደዚሁም ወደ ቤቱ አቅጣጫ፣ እዚያ እርሱ በአምላክ ስም የገነባ ወደሆነው ቤት ዞረው ማስገድ እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ይናገር ነበር፡፡ እንግዲህ ይህ የቂብላ ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡

*በዚያ ስሜ ይሆናል ወዳልኸው ስፍራ ወደዚህ ቤት ዓይኖችህ ሌሊትና ቀን የተገለጡ ይሁኑ፡፡ (ነገሥት ቀዳማዊ 8፡29)*

*ባሪያህና ሕዝብህ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ የሚጸልዩትን ልመና ስማ፣ በማደሪያህ በሰማይ ስማ፤ ሰምተህም ይቅር በል፡፡*

*(ነገሥት ቀዳማዊ 8፡30)*

*አንተን ስለበደሉ ሰማይ የተዘጋ ጊዜ፣ ዝናብም ባልዘነበ ጊዜ፣ ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩ፣ ስምህንም ቢያከብሩ፣ ባስጨነቅሃቸውም ጊዜ ከኃጢአታቸው ቢመለሱ አንተ በሰማይ ስማ፤*

*(ነገሥት ቀዳማዊ 8፡35)*

*ማናቸውም ሰው የልቡን ሕመም አውቆ ጸሎትና ልመና ቢጸልይ፣ እጆቹንም ወደዚህ ቤት ቢዘረጋ፤*

*(ነገሥት ቀዳማዊ 8፡38-39)*

*ከአሕዛብም ከእስራኤል ወገን ያልሆነ እንግዳ ታላቁን ስምህን፣ ብርቱይቱንም እጅህን፣ የተዘረጋውንም ክንድህን ሰምቶ ስለስምህ ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ፣ መጥቶም ወደዚህ ቤት በጸለየ ጊዜ፤ (ነገሥት ቀዳማዊ 8፡42-43)*

*አንተ በማደሪያህ በሰማይ ስማ፣ የምድርም አሕዛብ ሁሉ ስምህን ያውቁ ዘንድ እንደ አሕዛብም እንደ እስራኤል ይፈሩ ዘንድ፣ በዚህም በሠራሁት ቤት ስምህ እንደ ተጠራ ያውቁ ዘንድ፣*

*(ነገሥት ቀዳማዊ 8፡43)*

*ሕዝብህም ጠላቶቻቸውን ለመውጋት አንተ በምትልካቸው መንገድ ቢወጡ፣ አንተ ወደ መረጥሃት ከተማ፣ እኔም ስለስምህ ወደ ሠራሁት ቤት ለእግዚአብሔር ቢጸልዩ፣ ጸሎታቸውንና ልመናቸውን በሰማይ ስማ፣ ፍርድህንም አድርግላቸው፡፡ (ነገሥት ቀዳማዊ 8፡44)*

*(ምንጭ፡ www.quran-islam.org/.../qibla old and new)*

## ኢስላማዊው የሐጅ ሥነ-ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስ

የዚህ መጽሐፍ የጽሕፈት ሥራ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት የሚቀጥለው ጽሑፍ ካልታወቀ ምንጭ ወደኛ መጣ፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከኢስላማዊው "ሐጅና ዑምራ ሥነ-ሥርዓት" ጋር በምናመሳክርበት ጊዜ ይህ አስደናቂው/ተዓምራዊው መጣጣም እንደው እንደ ዕድል ያልተገኘ መሆኑን ደረስንበት፡፡ ይህን ወርቃማ መረጃ ላስተላለፉልን ለወንድም ሳይለንት ዊስደም እና ለባልደረባው አድናቆታችንን እየገለጽን እነዚያ የማስተዋልና

የመገሰጽ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች ያስተውሉትና ይገሰጹበት ዘንድ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማካተት ወደድን፡፡

*(የ)መጭውን ዓለም (ቅጣት) በመፍራትና የጌታውን እዝነት ተስፋ በማድረግ የሌሊቱን ሰዓቶች በሱጁድና በመቆም የሚያሳልፉ (ከከሀዲያን ጋር እኩል ናቸውን?) በላቸው፡፡ የሚገሰጹት የአዕምሮ ባለቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ (አል-ቁርኣን 39፡9)*

በሕዝቅኤል መጽሐፍ (ምዕ 40-47) ውስጥ ያን ለርሱ በጌታ (ወይም በመልአክ) የተደረገውን በራሱ ዕይታ ውስጥ አድርጎ ስለጉዞው ይነግረናል፡፡ ከርሱ የዚህ ጉዞ ገለፃ የሚከተሉትን ነጥቦች መደምደም እንችላለን፡-

*በተማረክን በሀያ አምስተኛው ዓመት በዓመቱ መጀመሪያ ከወሩ በአስረኛው ቀን፣ ከተማይቱ ከተመታች በኋላ በአስራ አራተኛው ዓመት፣ በዚያው ቀን የእግዚአብሔር እጅ በኔ ላይ ነበረ፣ እርሱም ወደዚያ ወሰደኝ፡፡ (ሕዝቅኤል 40፡1-2)*

*በእግዚአብሔር ራዕይ ወደ እስራኤል ምድር አመጣኝ፣ እጅግም በረዘመ ተራራ ላይ አኖረኝ፣ በዚያም ላይ በደቡብ ወገን እንደ ከተማ ሆኖ የተሠራ ነገር ነበር፡፡ (ሕዝቅኤል 40፡2-3)*

ፀሐፊው በራሱ አመለካከት እነዚህን ሁለቱን የሕዝቅኤል ጥቅሶች ከሐጅና ዑምራ የአምልኮ ሥርዓቶች ጋር ያዛምዳቸዋል፤ የዚህ ጉዞ ወቅት (በዓመቱ መጀመሪያ፣ ከወሩ በአስረኛው ቀን) እንደመሆኑ መጠን፡፡ ይህም ከኢስላማዊው በዓል ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡ አይሁዶች ልክ እንደ ሙስሊሞች የጨረቃ ዘመን አቆጣጠርን ይጠቀሙ ነበር፡፡ እናም የመጨረሻው ወር አስረኛው ቀን ዒድ አል አድሃ ነው፡፡ ወደ መካም ሐጅ የሚደረግበት ወቅት እንደሆነ በሚገባ ይታወቃል፡፡

*ነገር ግን የእስራኤል ልጆች ከእኔ ዘንድ በሳቱ ጊዜ የመቅደሴን ሥርዓት የጠበቁ የሳዶቅ ልጆች ሌዋውያን ካህናት ያገለግሉኝ ዘንድ ወደ እኔ ይቀርባሉ፣ ስቡንና ደሙንም ወደ እኔ ያቀርቡ ዘንድ በፊቴ ይቆማሉ፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡15)*

*ወደ መቅደሴም ይገባሉ፣ ያገለግሉኝም ዘንድ ወደ ገበታዬ ይቀርባሉ፣ ሥርዓቴንም ይጠብቃሉ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡16-17)*

*ወደ ውስጠኛውም አደባባይ በር በገቡ ጊዜ የተልባ እግር ልብስ ይልበሱ፤ በውስጠኛውም አደባባይ በርና በቤቱ ውስጥ ባገለገሉ ጊዜ ከበግ ጠጉር አንዳች ነገር በላያቸው አይሁን፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡17-18)*

*በራሳቸው ላይ የተልባ እግር መጠምጠሚያ ይሁን፣ በወገባቸውም ላይ የተልባ እግር ሱሪ ይሁን፣ የሚያወዛም ነገር አይታጠቁ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡18)*

*ወደ ውጭውም አደባባይ ወደ ሕዝብ በወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፣ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩ፣ ሕዝቡንም በልብሳቸው እንዳይቀድሱ ሌላውን ልብስ ይልበሱ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡19-20)*

*ካህናቱም ሁሉ በውስጠኛው አደባባይ ሲገቡ የወይን ጠጅ አይጠጡ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡21-22)*

ደህና፣ የነዚህ ጥቅሶች ሥዕላዊ ገለፃ በሚገባ ግልጽ ነው፡፡ መተርጎም አይስፈልግም፡፡ እንዲሁ ለአስተያየት ያህል፡- ሕዝቅኤል ሑጃጆችን (ሐጅ አድራጊዎችን) "ሌዋውያን ካህናት" ሲል ጠርቷል፡፡ ያ የሆነው የእስራኤል ልጆች ከአምላክ መንገድ ጠምመው የሄዱ ጊዜ ነው፡፡ (ስለዚህ እነርሱ "ሑጃጆቹ/ ሐጅ አድራጊዋቹ" ከእስራኤላውያን አይደሉም፡፡)

እነርሱ ወደ ውስጠኛው አደባባይ የገቡ ጊዜ ልብሳቸውን ገልጽዋል፡- *“ወደ ውስጠኛውም አደባባይ በር በገቡ ጊዜ የተልባ እግር ልብስ ይልበሱ፤ በውስጠኛውም አደባባይ በርና በቤቱ ውስጥ ባገለገሉ ጊዜ ከበግ ጠጉር አንዳች ነገር በላያቸው አይሁን፡፡ በራሳቸው ላይ የተልባ እግር መጠምጠሚያ ይሁን፣ በወገባቸውም ላይ የተልባ እግር ሱሪ ይሁን፡፡”* እነዚህ በትክክል የሙስሊም ሑጃጆች (ሐጅ አድራጊዎች) አልባሳት ናቸው…!

ሑጃጆችን የሚገልጽ ተጨማሪ ማብራሪያ አለ፡- *“ወደ ውጭውም አደባባይ ወደ ሕዝብ በወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፣ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩ፣ ሕዝቡንም በልብሳቸው እንዳይቀድሱ ሌላውን ልብስ ይልበሱ፡፡”* እናም ይህ “ኢሕራም” ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡

**ማጠቃለያ፡-** “ሕዝቅኤል በሐጅ *ሥነ-ሥርዓት* ላይ ነበር (ቢያንስ ዑምራ ላይ)” … ያ ሰ..ላ…ም…!

***እንዲህም አለኝ፡- በልዩ ስፍራ አንፃር በሰሜንና በደቡብ በኩል ያሉ ዕቃ ቤቶች፣ እነርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ካህናት ከሁሉ ይልቅ የተቀደሰውን ምግብ የሚበሉባቸው ቤቶች ናቸው፡፡ ስፍራው ቅዱስ ነውና በዚያ የተቀደሰውን ነገር የእህሉን ቁርባን የኃጢአቱንና የበደሉን መስዋዕት ያኖራሉ፡፡***

***(ሕዝቅኤል 42፡13)***

***ካህናቱም በገቡ ጊዜ ከመቅደሱ በውጭው አደባባይ አይወጡም፣ የሚገለገሉበትን ልብሳቸውን ግን ቅዱስ ነውና በዚያ ያኖሩታል፣ ሌላም ልብስ ለብሰው ወደ ሕዝብ ይወጣሉ፡፡***

***(ሕዝቅኤል 42፡14)***

ሕዝቅኤል በነዚህ ጥቅሶች በሐጅ ወቅት የሚደረገውን መስዋዕት እየጠቀመን ነው፡- *“የእህሉን ቁርባን የኃጢአቱንና የበደሉን መስዋዕት ያኖራሉ፡፡”*

ከዚህም በተጨማሪ በሐጅ መጀመሪያ ላይ ስለአል-ኢሕራም ይናገራል… *“የሚገለገሉበትን ልብሳቸውን ግን ቅዱስ ነውና በዚያ ያኖሩታል፣ ሌላም ልብስ ለብሰው ወደ ሕዝብ ይወጣሉ፡፡”* እነዚህ በርሱ 44፡17-19 ውስጥ የተብራሩ አልባሳት ናቸው፡፡

*ጠቃሚ ማስታወሻ፡-* በዚህ ጉዞ ወቅት ሕዝቅዔል ስፍራውንና ልኬቱን ልብ እንዲል በአምላክ ተነግሮታል፡፡ … እስቲ እናንብብ፡-

***እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፡- የሰው ልጅ ሆይ፣ ልብ አድርግ ስለ እግዚአብሔርም ቤት ሥርዓትና ሕግ ሁሉ የምናገርህን ሁሉ በዓይንህ ተመልከት በጆሮህም ስማ፣ የቤቱንም መግቢያ የመቅደሱንም መውጫ ሁሉ ልብ አድርግ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡5)***

***ለዓመጸኛው የእስራኤል ቤት እንዲህ በል፡- ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ርኩሰታችሁ ሁሉ ይብቃችሁ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፡6-8)***

ነገር ግን አምላክ የዚህ ዓይነት ነገር ለምን ይላል? ምላሹ ከአል-ቁርኣን ይገኛል፡፡ በሱረህ (ምዕራፍ) አል-በቀራህ (ላም፣ ምዕራፍ 2)፣ እንዲህ እናነባለን፡-

***የፊትህን ወደ ሰማይ መገላመጥ (በቂብላ ፍለጋ እይታህን ወደላይ ማንጋጠጥ) እናያለን፡፡ ወደምትወዳት ቂብላ እናዞርሃለን፡፡ ፊትህን ወደተከበረው መስጂድ (መስጂድ አል-ሐራም) አዙር፡፡ የትም ቦታ ሆናችሁ ፊታችሁን ወደርሱ አቅጣጫ አዙሩ፡፡ እነዚያ መጽሐፉን የተሰጡ ወገኖች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) እርሱ (የቂብላው ለውጥ) ከአላህ የሆነ እውነት መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ አላህ ከሚሠሩት ዘንጊ አይደለም፡፡(አል-ቁርኣን 2፡144)***

የቂብላ መለወጥ ጉዳይ ለሙስሊሞች በጣም ግራ አጋቢ ነበር፡፡ በመዲና የነበሩ አይሁዶች ያን ለግል ፍላጎታቸው ተጠቀሙበት፡፡ ግና እንዲህም ሆኖ አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) በአል-

ቁርአን ውስጥ አጋላጣቸው፡፡ አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) በግልጽ እንዲህ ይላል፡- *"እነዚያ መጽሐፉን የተሰጡ ወገኖች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) እርሱ (የቂብላው ለውጥ) ከአላህ የሆነ እውነት መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡"* ከዚህ የተነሳ አምላክ ሕዝቅኤልን ስፍራውንና መገለጫውን ልብ እንዲያደርግ በማዘዝ በራሳቸው መጽሐፍት ውስጥ በነርሱ ላይ ማስረጃ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በርግጥ መጽሐፍቱ ከተበረዙ በኋላ እንኳን ማስረጃው እንዳለ ዘልቋል፡፡ *"እነርሱ ከአምላክ ቀድመን ብዙ ሄደናል ብለው ያስባሉ፤ ግና አምላክ እነርሱን በሁሉም ነገር ያካክባቸዋል፡፡"*

በየዓመቱ … እዚያ ያለው ጉዳይ የፈለገው ይሁን በሁለቱ ዕለታት (ዒድ አል አድሃ እና የሕዝቅኤል ጉዞ) መካከል መመሳሰሎች አሉ፡፡ … የተቀረው ታሪክ ነገሮችን የበለጠ ግልጽ ያደርጋቸዋል፡፡

ቦታውን በተመለከተ? ደህና! እስቲ እናንብብ፡-

***በእግዚአብሔር ራዕይ ወደ እስራኤል ምድር አመጣኝ፣ እጅግም በረዘመ ተራራ ላይ አኖረኝ፣ በዚያም ላይ በደቡብ ወገን እንደ ከተማ ሆኖ የተሠራ ነገር ነበር፡፡ (ሕዝቅኤል 40፡2-3)***

*"ከተማዋ ከእስራኤል ምድር በስተ ደቡብ ናት፣ እዚያ በተራራዎች የታጠረች"* ይህች ከተማ ማን ናት? ያለ ምንም ጥርጥር መካ ከእስራኤል ምድር በስተ ደቡብ ትገኛለች፡፡ እንደዚሁም በተራራዎች የተከበበች ናት፡፡ አሁንም ያንን ቦታ በመግለጽ ረገድ የሕዝቅኤል ተጨማሪ ማስረጃዎች በሚቀጥለው ርዕስ "ካዕባ በመጽሐፍ ቅዱስ" በሚለው ሥር ይገለጻሉ፡፡

## ካዕባ በመጽሐፍ ቅዱስ

በሒጃዝ ግዛት በዐረቢያ ደቡባዊ ክፍል፣ ከቀይ ባሕር እሩቅ ሳይሆን የመካ ከተማ ትገኛለች፡፡ በዚህች ከተማ እምብርት ላይ ከድንጋይ የተሠራ ትንሽ አራት ማዕዘን ግንባታ ይገኛል፡፡ ወደ 60 ጫማ ርዝመት፣ 60 ጫማ ወርድ እና 60 ጫማ ቁመት ይሆናል፡፡ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ይህች ከተማና ይህ ከድንጋይ የተሠራ ቤት ለዓለም ተጓዦች ይታወቁ ነበር፡፡ ይህ በይቱሏህ ነው፣ የአላህ ቤት፡፡ ቅዱስነቱና ጥንታዊነቱ ከታሪክ ከራሱ የበለጠ ጥንት ነው፡፡

ካዕባ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው ቅርጹ አራት ማዕዘን ነው፡፡



ሕዝቅኤል የዚያን ስፍራ ቅርጽ ሲገልጽ፡-

***ውስጠኛውንም ቤት ለክቶ በፈጸመ ጊዜ ወደ ምስራቅ በሚመለከት በር መንገድ አወጣኝ፣ እርሱንም በዙሪያ ለካው፡፡ (ሕዝቅኤል 42፡15)***

*የምስራቁን ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ፡፡ ዞረም፣ (ሕዝቅኤል 42፡16)*

*የሰሜኑንም ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ፡፡ ዞረም፣ (ሕዝቅኤል 42፡17)*

*የደቡቡንም ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ፡፡ ዞረም፣ (ሕዝቅኤል 42፡18)*

*የምዕራቡንም ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ፡፡ ዞረም፣ (ሕዝቅኤል 42፡19)*

*በአራቱ ወገን ለካው፡፡ የተቀደሰውንና ያልተቀደሰውን ይለይ ዘንድ ርዝመቱ አምስት መቶ ክንድ፣ ወርዱም አምስት መቶ ክንድ የሆነ ቅጥር በዙሪያው ነበረ፡፡ (ሕዝቅኤል 42፡19-20)*

ከዚህ ቅርጽ አንፃር ይህ ቦታ አራት ማዕዘን ነው፡፡

*በመቅደሱም ፊት ርዝመቱን ሀያ ክንድ፣ ወርዱንም ሀያ ክንድ አድርጎ ለካና፡- ይህ ቅድስተ ቅዱሳን ነው አለኝ፡፡ (ሕዝቅኤል 41፡4)*

እንደዚህ ቅዱስ ቦታ አገላለጽ ከሆነ ቅርጹ አራት ማዕዘን ነው፡፡ እንደዚሁም ካዕባ እንዲሁ አራት ማዕዘን ግንብ እንደሆነ በሚገባ ይታወቃል፡፡ … ለመሆኑ በክርስትና ወይም በአይሁድ ማንኛውም የተቀደሰ ቤት ሆኖ ተመሳሳይ ቅርጽ ያለው አለን? በተጨማሪም ሕዝቅኤል የቤቱን መስፋፋት ተንብየዋል፡፡ እስቲ እናንብበው፡-

*በመቅደሱም ግንብ ዙሪያ ደገፋዎች ይሆኑ ዘንድ አረፍቶች ነበሩ፣ በመቅደሱም ግንብ ውስጥ ደገፋዎች አልነበሩም፡፡ በቤቱም ዙሪያ ባለ ግንብ ውስጥ በነበሩት አረፍቶች ምክንያት ላይኞቹ ጓዳዎች ከታችኞቹ ጓዳዎች ይበልጡ ነበር፡፡ (ሕዝቅኤል 41፡6-7)*

*ወደ መቅደሱም መዝጊያ መለሰኝ፣ እነሆም፣ ውኃ ከቤቱ መድረክ በታች ወደ ምሥራቅ ይወጣ ነበር፣ የቤቱ ፊት ወደ ምስራቅ ይመለከት ነበርና ውኃውም ከቤቱ ከቀኝ ወገን በታች በመሠዊያው በደቡብ በኩል ይወርድ ነበር፡፡ (ሕዝቅኤል 47፡1)*

*በሰሜኑም በር በኩል አወጣኝ በስተ ውጭ ባለው መንገድ ወደ ምስራቅ ወደሚመለከት በስተ ውጭ ወዳለው በር አዞረኝ እነሆም፣ ውኃው በቀኝ ወገን ይፈስ ነበር፡፡ (ሕዝቅኤል 47፡2)*

*ሰውዬውም ገመዱን በእጁ ይዞ ወደ ምስራቅ አንድ ሺህም ክንድ ለካ፣ በውኃውም ውስጥ አሻገረኝ፣ ውኃውም እስከ ቁርጭምጭሚት ደረሰ፡፡ (ሕዝቅኤል 47፡3-4)*

*ደግሞ አንድ ሺህ ለካ በውኃውም ውስጥ አሻገረኝ፣ ውኃውም እስከ ጉልበት ደረሰ፡፡ ደግሞ አንድ ሺህ ለካ በውኃውም ውስጥ አሻገረኝ፣ ውኃውም እስከ ወገብ ደረሰ፡፡ (ሕዝቅኤል 47፡4)*

*ደግሞ አንድ ሺህ ለካ ልሻገረውም የማልችለው ወንዝ ሆነ፣ ውኃውም ጥልቅ ነበረ፣ የሚዋኙበትም ውኃ ነበረ፣ ሰው ሊሻገረው የማይችለው ወንዝ ነበር፡፡ (ሕዝቅኤል 47፡5)*

ደህና፣ በነዚህ አንቀጾች ሕዝቅኤል በቤቱ ዙሪያ መሂዱን እየተናገረ ነው፡፡ እንደዚሁም በትክክል ከሙስሊም የሐጅ ሥነ-ሥርዓት በጎን በኩል፣ ነገር ግን ከቤቱ ሥር ውኃን አገኘ፣ ምን ዓይነት ውኃ?...

ይህ በጣም ጥልቅ ውኃ ከቤቱ ሥር ከቀኝ ወገንና ከመሰዊያው ደቡብ በኩል የሚወርድ ሲሆን (ወደፊት የሚብራራ ይሆናል)…!

የርሱ የዚህ ውኃ ማብራሪያና እንዴት ጥልቅ እንደነበረ የገለጸበት ሁኔታ ይህ ልክ የዘምዘም ውኃን ያሳያል… የዘምዘም

ውኃ በመካና በዙሪያ ባሉ ስፍራዎች ግልጋሎት ላይ ከዋለ አሁን ከ1400 ዓመታት በላይ ሆኗል፡፡ አሁንም በጥሩ ሁኔታ ጥልቅ (በርካታ) ነው…!

የሕዝቅኤልን የውኃ ማብራሪያ በተመለከተ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

*"አላህ በእስማዔል እናት ላይ እዝነቱን ያውርድ! ዘምዘምን ትታው ቢሆን ኖሮ (እርሱን ለመቆጣጠር ሙከራ ሳታደርግ ቢፈስ ኖሮ) (ወይም እርሷ ከዚያ ውኃ ባትዝቀው ኖሮ) (ማለትም የውኃ ዕቃዋን ለመሙላት) ዘምዘም በምድር ገጽ ላይ የሚፈስ ምንጭ ይሆን ነበር፡፡"*

*"ደግሞ አንድ ሺህ ለካ ልሻገረውም የማልችለው ወንዝ ሆነ፣ ውኃውም ጥልቅ ነበረ፣ የሚዋኝበትም ውኃ ነበረ፣ ሰው ሊሻገረው የማይችለው ወንዝ ነበር፡፡"… (ሕዝቅኤል 47፡5)*

ከላይ ያለው የአምላክ ቤት ማብራሪያ በሰለሞን የተገነባውን ቤተ መቅደስ በትክክል ያመለክታልን? ምላሹ "አይደለም" ነው፡፡ እስቲ የሰለሞንን ቤተ መቅደስ ከካዕባ ጋር እንደሚከተለው ሁኔታ እናነጻጽር፡-

*ንጉሡ ሰለሞንም ለእግዚአብሔር የሠራው ቤት ርዝመቱ ስድሳ ክንድ፣ ወርዱም ሀያ ክንድ፣ ቁመቱም ሠለሳ ክንድ ነበረ፣*
*(ነገሥታት ቀዳማዊ 6፡2)*

ነገር ግን ካዕባ ርዝመቱ ወደ 60 ጫማ፣ ወርዱ 60 ጫማና ቁመቱም 60 ጫማ ነው፡፡

እንደ ሰለሞን ቤተ መቅደስ ገለፃ ከሆነ፣ ከዚያ በሕዝቅኤል 40-43 ከተገለጸው እንደሚለይ በደንብ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ሕዝቅኤል ማንኛውንም በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የአምላክ ቤት ነው የገለጸው

ተብሎ የሚነሳውን የክርክር ሙከራዎች ሁሉ ከንቱ ያደርጋል፤ ምክንያቱም አራት ማዕዘን ቤት አልነበረምና፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን አራት ማዕዘን ቤት ከካዕባ ውጭ በምድር ገጽ ላይ የት እውን እንደሆነ መለየት የሚችል አለን?

## አንተስ ታውቀዋለህ?

### *እኚህን ሰው ማወቅ ያስፈልግሃል፣ እኚህ ሰው ማናቸው?*

በሂስ መልክ የሚቀርብ ምስል ሠሪዎች (ካርቱኒስት) የርሳቸውን አስቂኝ ምስሎች ሠርተዋል፡፡ ብልህ ሰዎች እርሳቸውን ታላቅ ሰው በማለት አወድሷቸዋል፡፡ ከ1.5 ቢሊዮን ሕዝብ በላይ እርሳቸው የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መስክረዋል፣ ይመሰክራሉም፡፡

### ኢንሳይክሎፒዲያ ቢሪታኒካ

"… በብዙ በጥንት ምንጮች ውስጥ ያለው ሰፊ እውነታ እርሱ ታማኝና ቀጥተኛ ሰው መሆኑን ያሳያል፣ እርሱ ያ የሌሎችን፣ እነርሱም ልክ በተመሳሳይ ሁኔታ ታማኞችና ቀጥተኛ የነበሩ ሰዎችን ክብርና ታማኝነትን ያገኘ ነው፡፡" (ቅጽ 12)

**ሙሐመድ** ከሁሉም ነብያትና ሃይማኖታዊ ሰዎች በጣም ስኬታማ የሆነው ነው፡፡"

### ጆርጅ በርናንድ ሾው

➔ እኔ ሁል ጊዜ ለሙሐመድ ሃይማኖት ከፍተኛ ግምት አለኝ፤ ምክንያቱም በጣም አስገራሚ ከሆነው አስፈላጊነቱ የተነሳ፡፡ እርሱ ብቸኛው ሃይማኖት ነው፡፡ ያ

ለተለዋዋጭ የህይወት ደረጃ የመዋሃድ ችሎታ ያለው እምነት በመሆኑ ለኔ የሚታየኝ፣ በሁሉም ወቅት የዕድሜ ክልል ራሱን ማዘጋጀት እንደሚችል ነው፡፡

- ➔ እርሱን አጠናሁት፣ "ግሩም ሰው እና በኔ አመለካከት ፀረ-ክርስቶስ ከመሆን የራቀ ነው፣ እርሱ የመላው የሰው ልጆች አዳኝ ተብሎ ሊጠራ ይገባል፡፡"

- ➔ "እኔ እንደማምነው እርሱን የሚመስል ሰው የዘመናዊውን ዓለም አምባገነንነት የሚገዛ ከሆነ፣ በዚያ በጣም ተፈላጊ የሆነውን ሰላምና ደስታን ማምጣት በሚችልበት መንገድ ችግሮቹን በመፍታት ስኬታማ ይሆን ነበር፡፡"

- ➔ "እኔ ስለሙሐመድ እምነት የምተነብየው፣ ለነገው አውሮፓ ተቀባይነት አለው፣ ልክ በዛሬው አውሮፓ ተቀባይነትን ማግኘት እንደጀመረው ሁሉ፡፡"

- ➔ "በሚቀጥሉት መቶ ዓመታት ውስጥ ማንኛውም ሃይማኖት እንግሊዝን ለመግዛት፣ አውሮፓን ሳይቀር፣ ዕድል ቢኖረው እርሱም ኢስላም ብቻ ይሆናል፡፡"

(ሰር ጆርጅ በርናርድ ሾው በ "እውነተኛው ኢስላም" ቅጽ 1፣ ቁጥር 8፣ 1936 እ.ኤ.አ)

## እርሱ ተግብሮታል![16]

- ➔ እርሱ እዚህ ምድር ላይ ከተራመዱት ሰዎች በጣም እርግጠኛ በሆነ ሁኔታ የሚደነቅ ሰው ነበር፡፡

- ➔ እርሱ ሃይማኖትን ሰብኳል፣ ግዛቶችን መስርቷል፣ ሕዝብን ገንብቷል፣ የሥነ-ምግባር ደንቦችን ዘርግቷል፣ በርካታ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን በመሪነት ጀምሯል፡፡

---

[16] የአዘጋጁ ማስታወሻ

➔ የርሱን አስተምህሮ እንዲተገብሩና እንዲወክሉ ኃያልና ታታሪ ማህበረሰብን መሥርቷል፣ እንደዚሁም ወደፊት ለሚመጣው ለሁል ጊዜ የሰውን አስተሳሰባዊና ባህሪያዊ ዓለማትን ሙሉ በሙሉ ለውጧል፡፡ አዎ! እርሱም ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነበር፡፡

## ተልዕኮው የማይቻል ነበር!

እርሱ የተወለደው በዐረቢያ በ570 ዓመት ነበር፣ የእውነትን ሃይማኖት የመስበክ ተልዕኮውን፣ ኢስላምን (ለአንድ አምላክ ብቻ እጅ መስጠትን/መታዘዝን) በአርባ ዓመቱ ጀመረ፡፡ እንዲሁም በስድሳ ሦስት ዓመቱ ከዚህ ዓለም ተለየ፡፡

በዚህች አጭር በርሱ 23 የነብይነት ዓመታት ውስጥ መላውን የዐረቢያ ባህረ ሰላጤ ለውጧል፡፡

➔ ከጣዖት አምልኮና ከተለያዩ የሽርክ ተግባራት ወደ አንድ እውነተኛ አምላክን ብቻ ማምለክ/መግገዛት/መታዘዝ፣

➔ ከጎሳ ግጭቶችና ጦርነቶች ወደ ብሔራዊ አንድነትና ውህደት፣

➔ ከአስካሪ መጠጥ ሱስና ወራዳነት ወደ አሳቢ መሆንና ሃይማኖተኝነት፣

➔ ከሕግ አልበኝነትና ብጥብጥ ወደ ሥርዓታዊ አኗኗር፣

➔ ከአነጋገር ክስረት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሥነ-ምግባር ክብር፣

የሰው ልጅ ታሪክ የዚህ ዓይነት የማህበረሰብ ወይም የስፍራ አጠቃላይ ሽግግርን/ለውጥን ከዚያ በፊት ወይም በኋላ ፈጽሞ አያውቀውም፡፡

→ *አስቡት! እነዚህ ሁሉ የማይታመኑ ድንቃ ድንቆች ልክ በሁለት ዐስርተ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ*

## ሊቀ መምህር/ ጸኃፊ ሪጊናልድ ቦስዎርዝ ስሚዝ

“እርሱ በአንድ ጊዜ ቄሳርና ሊቀ ጳጳስ ነበር፤ ግና እርሱ እንደ ሊቀ ጳጳስ የማያስመስል አለሁ አለሁ የማለት ባህሪ የሌለው፣ እንደ ቄሳር ክፍለ ጦር ወይም በርካታ ሕዝብ ሳይኖረው ቄሳር ነበር፡- ሕግ አስከባሪ፣ ቋሚ ሠራዊት ሳይኖረው፣ ያለ ዐጃቢ፣ ያለ ቤተ መንግስት፣ ውስን ገቢ የሌለው ነበር፡- ማንም ሰው በትክክለኛ መለኮታዊ መመሪያ እመራሁ የሚል መብት ካለው፣ እርሱ ሙሐመድ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ ያለ መሣሪያውና ያለደጋፊው ሁሉንም ኃይል ነበረው፡፡”

## ሚካኤል ኤች. ሐርት

እርሳቸውን ከሁሉም መርጦ አንደኛ ሲያደርጋቸው ይህን ብሎ ነበር፡-

“የዓለምን በጣም ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን ዝርዝር እንዲመራ የኔ የሙሐመድ ምርጫ የተወሰኑ አንባቢዎችን ሊያስገርም፣ እንዲሁም ምናልባትም በሌሎች ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ግና እርሱ በታሪክ ውስጥ በሁለቱም፣ በመንፈሳዊና በዓለማዊ ደረጃዎች በከፍተኛ ሁኔታ ስኬታማ የነበረ ብቸኛው ሰው ነው፡፡”

(ዘ ሀንድሬድ፡ ኤ ራንኪንግ ኦፍ ዘ ሞስት ኢንፍሉዌንሻል ፐርሰንስ ኢን ሂስትሪ፣ ኒው ዮርክ፣ 1987፣ ገጽ 33)

## ናፖሊን ቦናፓርቴ

እኔ ተስፋ የማደርገው ጊዜው ሩቅ እንደማይሆን ነው እኔና በሁሉም ሀገሮች የሚገኙ ብልህና የተማሩ ሰዎች በቁርአን መርህ

የተመሠረተ አንድ ወጥ ሥርዓት እንደሚመሠርቱና እነዚህም እውነተኛ መመሪያዎች ሰዎችን ወደ ደስታ የሚመሩ ናቸው፡፡

(ክርስቲያን ቼርፌልስ ቦና ፓርቴ ኤት ኢስላም ውስጥ በትምህርተ ጥቅስ ከሰፈረው የተወሰደ፣ (ፓሪስ 1914))

## ላማር ቲን

ታዋቂው የታሪክ ምሁር፣ ስለሰው ልጅ ታላቅነት አድናቆት አስፈላጊነት ሲናገር፡-

የዓላማ ታላቅነት፣ ያንን ዓላማ ለማስፈጸም ያለው አቅም አናሳነትና የውጤቱ አስገራሚነት - ሦስቱ የሰው ልጆች የጉብዝና መስፈርት ከሆኑ፣ በዘመናዊው ታሪክ ውስጥ ማነው ማንኛውንም ታላቅ ሰው ከሙሐመድ ጋር ለማወዳደር መድፈር የሚችል?"

በጣም ታዋቂ ሰዎች ሠራዊቶችን፣ ሕጎችንና ግዛቶችን ብቻ መስርቷል ፡፡ ምንም ያህል ብመሰርቷቸውም እነዚህ ሁሉ ከቁሳዊ ኃይላት ያላለፉና ብዙውን ጊዜ በዓይኖቻቸው ፊት የሚናዱ ነበሩ፡፡ እነርሱ ሁሉም ነገር ሙሉ በሙሉ ከሆነም መስርተዋል፣ ቢሆኑም ከቁሳዊ ኃይላት የበለጡ አልነበሩም፣ እነዚያ በዓይኖቻቸው ፊት ብዙ ጊዜ የሚናዱ ይሆናሉ፡፡ ይህ ሰው ያንቀሳቀሰው ሠራዊቶችን፣ ሕጎችን፣ ግዛቶችን፣ ሕዝቦችንና ሥርወ መንግስታትን ብቻ አይደለም፣ ግና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን፣ በያኔው አንድ-ሦስተኛው የዓለም ክፍል ላይ ሰፍረው የነበሩትን፤ እንዲሁም ከዚያም የበለጠ፣ መሠዊያዎችን፣ አማልክትን፣ ሃይማኖቶችን፣ ሐሳቦችን፣ እምነቶችንና ነፍሶችን… አንቀሳቅሷል፡፡

ለድል ያለው ታጋሽነት፣ የርሱ ምኞት፣ ያ ለአንድ ሐሳብ እጅ የሰጠና በማናቸውም ሁኔታ ለግዛት አለመታገል፤ የርሱ ወሰን የለሽ ጸሎቶች፣ ከአምላክ ጋር የርሱ ምስጢራዊ ንግግሮች፣ የርሱ ሞትና ከሞተ በኋላ የርሱ አሸናፊነት፤ እነዚህ ሁሉ እውነቱን ያረጋግጣሉ ለሐሰተኛ አካል የሚገቡ ሳይሆን ነገር ግን ለጽኑ እምነት፣ እነዚያ

ህግን/ቀኖናን ለማደስ ለርሱ ኃይሉን የሰጡ ናቸው፡፡ ፈላስፋ፣ ሥነ-ነገር አዋኚ፣ ሐዋሪያ፣ ሕግ አውጪ፣ ተዋጊ/ጦረኛ፣ የአመለካከቶች ገዥ፣ የምክንያታዊ ቀኖና አዳሽ፣ የአምልኮ ያለ ምስል፣ የሀያ ምድራዊ ግዛቶችና የአንድ መለኮታዊ ግዛት መስራች ሲሆን፣ ያ ሙሐመድ ነው፡፡ ሁሉንም መለኪያዎች የሰው ልጅ ታላቅነት የሚለካበትን በተመለከተ፣ ምናልባት በሚገባ ልንጠይቅ እንችላለን፣ ለመሆኑ ከርሱ የበለጠ አንድም ታላቅ ሰው አለን?

(ምንጭ፡ አልፎንስ ዲ ላማር ታይን፣ ሂስቶሪ ዲ ላ ቱርኪ፣ ፓርስ፣ 1854፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 276-277)

## ዓለም የታላላቅ ሰዎች ስብዕና የራሷ ድርሻ ነበራት

ነገር ግን እነዚህ ፍትሐዊ ያልሆኑ መረጃዎች ናቸው፣ እነዚያ ራሳቸውን በአንድ ወይም ሁለት ሙያዎች ታዋቂ ያደረጉ፣ እንደ ሃይማኖታዊ አመለካከት ወይም ወታደራዊ መሪነት ያሉትን፡፡

የነዚህ የዓለም ታላላቅ ስብዕናዎች አኗኗሮችና አስተምህሮዎች በጊዜ ጭጋግ ውስጥ ተሸፍኗል፡፡ ስለነርሱ የትውልድ ጊዜና ቦታ፣ ስለሕይወታቸው ዘይቤና ሁኔታ፣ ስለአስተምህሮዎቻቸው ባህሪና ዝርዝር እንዲሁም የስኬት ወይም የውድቀት ደረጃና መለኪያ ብዙ ግምት አለ፡፡ የነዚህን ሰዎች አስተምህሮዎች ዳግም በትክክል መገንባት ለሰው ልጆች የማይቻል ነው፡፡

## ፕሮፌሰር ሀርግሮንጅ

“በኢስላም ነብይ የተመሠረተው የሕዝቦች ሊግ የዓለም አቀፍ አንድነትና የሰው ልጆች ወንድማማችነት መርሆ አስቀምጧል፣ በዚያ ዓይነት ዓለም አቀፋዊ መሠረቶች ላይ ለሌሎች ሕዝቦች የብርሃን ሻማን እንዲያሳዩ፡፡” እርሱ ይቀጥላል፡- … “እውነታው ያ ነው፣ የሕዝቦች ሊግ አመለካከትን እውን ከማድረግ አንፃር የዓለም ማንኛውም ሕዝብ ኢስላም ከሠራው ተመሳሳይ ማሳየት አይችልም፡፡”

## ኤድዋርድ ጊቦን እና ሲሞን ኦክሊ

"እኔ በአንድ አምላክ እና በሙሐመድ የአምላክ ሐዋሪያ አምናለሁ" ቀናና የማይለወጥ የኢስላም የሙያ ዘርፍ ነው፡፡" የመለኮታዊው አዕምሮአዊ ምስል በማናቸውም በሚታይ ጣዖት አልተዋረደም፣ የነብዩ ክብር ከሰው ልጅ መልካምነት መለኪያ ፈጽሞ ገደብን አላለፈም፣ እንዲሁም የርሱ የሕይወት መመሪያዎች ምስጋናውን/አድናቆቱን በምክንያታዊና በሃይማኖታዊ ሰንሰለቶች ውስጥ በጥብቅ ተቆጣጥሯል፡፡

(ሂስትሪ ኦፍ ዘ ሳራክን ኢምፓየርስ፣ ለንደን፣ 1870፣ ገጽ 54)

## ቶማስ ካርሊል

"ሂሮውስ ሂሮ ዎርሺፕ" በሚለው መጽሐፉ፡-

"በዚህ ልበቅን ሰው (ሙሐመድ) ዙሪያ የተቆለለት ሐሰቶች (የምዕራባውያን ስም ማጥፋት) እኛ ብቻ የምናፍርበት ነው … እንዴት አንድ ሰው ብቻውን ሆኖ፣ ተፋላሚ ጎሳዎችንና ዘላኖችን ከሁለት ዐስርተ ዓመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በጣም ኃያላንና ስልጡን ወደሆነ ሕዝብ መለወጥ ቻለ፤ … (ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው) በርሱ የተረጋጋ ታላቅ ስብዕናና ቅንነት ነበር፡፡ ከነዚያ ውስጥ አንድ እንኳን የማይችል ግና ቅን ከመሆን ውጭ፡፡ እርሱ ዓለምን ለመቀስቀስ ነበር፣ የዓለም ሠሪው ይህን እንዲያደርግ አዘዘው፡፡"

## ሰብአዊ ፍጡር ነበር[17]

ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከሰብአዊ ፍጡር የበለጠ ወይም ያነሰ ምንም ነገር አልነበረም፡፡ ግና እርሱ ሰው ነበር ከተከበረ ተልዕኮ ጋር፣ ያ የሰውን ልጆች አንድ ለማድረግ ለአንድና ብቸኛው አምላክ እንዲታዘዙና በአምላክ ትዕዛዛት ላይ ተመሥርቶ

---

[17] የአዘጋጁ ማስታወሻ

በጣም ተስማሚና ቀጥ ወዳለው የሕይወት መንገድ እነርሱን ሊያስተምር ነው፡፡ እርሱ ሁልጊዜ እንዲህ ሲል ራሱን ይገልፃል፡- “የአምላክ ባሪያና መልዕክተኛ” እናም እንደዚሁ የርሱ እያንዳንዱ ተግባር በርግጥ ይህን መሆኑን ያውጃል፡፡

ዓለም፣ ግለሰቦች እነዚያ የነርሱ አኗኗርና ተልዕኮዎች በአፈ ታሪክ ውስጥ የተጣሉ ወደ መለኮታዊነት ከፍ ለማለት አልተሰላቸችም፡፡በታሪካዊ አነጋገር፣ ከነዚህ አፈታሪኮች አንዳቸውም ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የፈጸመውን ክፍልፋይ እንኳን አላሳኩም፡፡ እንደዚሁም የርሱ ሁሉም ትግሎች የነበሩት ለዋናው ዓላማ፣ የሰው ልጆች በመልካም የሥነ-ምግባር ደንቦች ላይ ሆነው አንድ አምላክን ብቻ እንዲያመልኩ አንድ ማድረግ ነው፡፡

ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በዚህ ዓይነት የተለያዩ የሰው ልጆች አስተሳሰባዊና ባህሪያዊ መስኮች በተሟላ ሁኔታ በተቀጣጠለው በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ይህን ሁሉ ፈጸመ፡፡

እያንዳንዱ የርሱ የግል ሕይወትና ሕዝባዊ ንግግሮች ዝርዝር በትክክል ተመዝግቧል፣ እንደዚሁም በታማኝነት እስከ እኛ ቀን ተጠብቋል፡፡ እነዚህ የተጠበቁ መዝገቦች ትክክለኛነታቸው ተመስክሮላቸዋል፣ በታማኝ ተከታዮቻቸው ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በርሱ ሚዛናዊ ያልሆኑ ተቺዎች ሳይቀር፡፡

## ማሃትማ ጋንዲ

በ “ያንግ ኢንዲያ” እንዲህ ይላል፡-

“እኔ ለማወቅ ፈልጌ ነበር፣ ከምርጦች አንዱ ያ የዛሬውን የማያጠራጥር ተጽእኖ በሚሊዮኖች የሰው ልጆች ልቦች ውስጥ ተቆጣጥሮ ያኖረ… በእርግጠኝነት የምናገረው እኔ እርግጠኛ ከመሆን የበለጠ ሆንኩኝ፣ ያም በሕይወት ሥርዓት ውስጥ በነዚያ ቀናት ለኢስላም ስፍራ ያገኘው ቦታውን የሸፈነው በሰይፍ

አልነበረም፡፡ ጥብቅ ቀናነት፣ የነብዩ ፍጹም ራስ ወዳድ አለመሆን፣ ቃል መግባትን በተመለከተ ከፍ ያለ ጥንቁቅነት፣ የርሱ ደፋርነት፣ የርሱ አለመፍራት፣ የርሱ በአምላክና በራሱ ተልዕኮ ላይ ያለው ፍጹም እምነት ነበር፡፡"

## ሳሮጂኒ ናይዱ

ታዋቂዋ ሕንዳዊት የቅኔ ሴት እንዲህ ትላለች፡-

"የመጀመሪያው ሃይማኖት ነበር ያ ዲሞክራሲን የሰበከውና የተገበረው፤ ምክንያቱም በመስጂድ ውስጥ፣ የሶላት ጥሪ የተሰማና አምላኪዎች የተሰበሰቡ ጊዜ፣ገበሬውና ንጉሱ ጎን ለጎን ተንበርክከው "ታላቅ አምላክ ብቻ ነው" ብለው ሲያውጁ የኢስላም ዲሞክራሲን በቀን ውስጥ አምስት ጊዜ ይተገብራሉ ፡፡"

(ኤስ. ናይዱ፣ አይድልስ ኦፍ ኢስላም፣ ቫይድ ስፒችስ ኤንደ ራይቲንግስ፣ ማድራስ፣ 1918)

## አን-ኒ በሳንት

በ "ሙሐመድ ሕይወትና አስተምህሮ" ውስጥ እንዲህ ትላለች፡-

"ለዚያ የታላቁን የዐረቢያ ነብይ ሕይወትና ባህሪይ ለሚያጠና ለማንም ሰው የማይቻል ነው ... ምንም ነገር ሊሰማው፣ ግና ለዚያ ኃያል ነብይ ውዳሴ እንጂ፣ ከኃያሉ አምላክ መልዕክተኞች አንዱና ታላቅ ለሆነው፡፡ እንዲሁም በዚያ እኔ ለናንተ ባስቀመጥኩት እንኳን እኔ ብዙ ነገሮችን መናገር እችላለሁ ምናልባትም ለናንተ እንግዳ ያልሆኑ ሲሆኑ፣ አሁን እኔ ራሴን ይሰማኛል አዲስ የአድናቆት መንገድ፣ አዲስ የውዳሴ ስሜት ለዚያ ለኃያሉ የዐረቢያ አስተማሪ በማናቸውም ጊዜ መልሼ ሳነባቸው፡፡"

ዛሬ አስራ አራት ክ/ዘመናት ካለፉ በኋላ የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሕይወት አስተምህሮዎች ያለ በጣም አነስተኛ መጓደል፣ ያለ ምንም ለውጥ ወይም ጣልቃ ገብነት ሕያው ሆነዋል፡፡ የሰው ልጆችን በርካታ በሽታዎች ለማከም፣ እነርሱ እርሱ በሕይወት እንዳለ እንደሠሩት ዛሬም ተመሳሳይ የማይሞት ተስፋ ያበረክታሉ፡፡…

ይህ የሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ተከታዮች የይገባኛል ክርክር አይደለም፣ ግና እንዲሁ ሊሸሹት የማይቻል መደምደሚያ፣ በዚያ ወሳኝና የማያዳላ በሆነ ታሪክ በኃይል ወይም በግዴታ የተደረገ/የተጫኔ ነው፡፡

ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አስተማሪ፣ ማሕበራዊ አሻሻይ/አዳሽ/ለዋጭ፣ የሥነ-ምግባር መማሪያ፣ አስተዳደራዊ ግዙፍነት፣ ታማኝ ጓደኛ፣ ግሩም ባልደረባ፣ አፍቃሪ ባል፣ አፍቃሪ አባት - ሁሉንም በአንድ ነበር፡፡

ከነዚህ የተለያዩ የሕይወት ሁኔታዎች በየትኛውም በታሪክ ሌላ ማንም ሰው መቼም እርሱን ፈጽሞ መብለጥ ወይም ከርሱ ጋር እኩል መሆን አይችልም፡፡ ግና ለሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንደዚህ ዓይነት የማይታመኑ ፍጹምነቶችን ለማሳካት ራስን ያለመውደድ ስብዕና ብቻ ነበር፡፡

## ላን ፑል

"የነብዩ ንግግሮችና የጠረጴዛ ውይይት" በሚለው ውስጥ፡-

የነዚያ እርሱ የጠበቃቸው ሰዎች በጣም ታማኙ ጠባቂ ነበር፡፡ በውይይት ውስጥ በጣም ጣፋጭና በጣም ተግባቢ ነበር፡፡ እነዚያ እርሱን ያዩት በድንገት በውዳሴ ይሞላሉ፤ እነዚያ እርሱ አጠገብ የመጡት እርሱን ወደዋል፤ እነዚያ እርሱን የሚገልጹት እንዲህ ይላሉ፡- "እኔ የርሱን አምሳያ ከዚህ በፊት ወይም በኋላ

ፈጽሞ አላየሁም፡፡" እርሱ የታላቅ ዝምታ ባለቤት ነበር፣ ግና የተናገረ ጊዜ በአጽንኦትና በጥንቃቄ ነበር፣ እናም ማንም ሰው እርሱ የተናገረውን መርሳት አይችልም …

## ዋሺንግተን ኢርቪንግ

የርሱ ወታደራዊ ድሎች፣ በራስ ወዳድነት ዓላማዎች ተጽዕኖ ውስጥ ገብተው ቢሆኑ ኖሮ እንደሚያደርጉት፣ ኩራትም ሆነ ከንቱ ግብዝነትን አልቀሰቀሰም፡፡ በርሱ የኃያልነት ጊዜ ውስጥ እርሱ ተመሳሳይ የባህሪ ቀናነትና ምግባር ጠብቆ ዘልቋል ልክ በርሱ የመከራ ቀናት እንደነበሩት፡፡ ለርሱ ከሚገባው በላይ ክብርን መስጠት የሚያስከፋው ነበር፡፡ እስካሁን ድረስ ንጉሳዊ ግዛትን ተጽእኖ ውስጥ ከማድረጉ ጋር ወደ ክፍል በሚገባበት ጊዜ ለርሱ ማንኛውም ያልተለመደ ስለክብሩ ውዳሴ ለርሱ በሌሎች ከታየው እርሱ ይከፋል፡፡

## ፕሮፌሰር ጁለስ ሜሰርማን

የአሜሪካ የአዕምሮ ሕክምና ማህበር፡-

ሊውስ ፓስተርና ሰልክ የመሳሰሉ ሰዎች በመጀመሪያ ትርጉም ውስጥ መሪዎች ናቸው፡፡ ጋንዲና ኮንፊኪየስ የመሳሳሉ ሰዎች፣ በአንድ ጎን በኩል፣ እነ አሌክሳንደር፣ ቄሳርና ሂትለር በሌላ ጎን በኩል፣ በሁለተኛና ምናልባትም በሦስተኛ ትርጉም መሪዎች ናቸው፡፡ ኢየሱስና ቡድሃ ብቻቸውን ከሦስተኛው ምድብ ይካተታሉ፡፡ ምናልባትም የሁልጊዜ ታላቅ መሪ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነበር፣ ያ ሁሉንም ሦስቱንም ሥራዎች በአንድነት ያዋሃደ፡፡ በዝቅተኛ ደረጃ፣ ሙሴ ተመሳሳይ ነገርን ሠርቷል፡፡

አሁን እባካችሁ ትንሽ ዘና በሉ …

እስቲ ላፍታ እናስብ …

እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ ....

እንደ አሳቢና ይመለከተኛል ባይ የሰው ልጅ አንተ ማድረግ የምትችለው በጣም ዝቅተኛው ነገር ቆም ማለትና ራስህን መጠየቅ ነው፡- እነዚህ በጣም ድንቅና አብዮተኛ የሆኑ የጥልቀት መለኪያ አባባሎች በርግጥ እውነት ይሆናሉ? እነሱ በርግጥ እውነት ናቸው፣ አንተም ይህን ሰው ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) አውቀህዋልን አታውቀውም ወይም ስለርሱም የሰማ አልነበርክም ብለህ በመገመት አንተ ለዚህ ትልቅ ፈተና ምላሽ የምትሰጥበትና እርሱን ለማወቅ የተወሰነ ጥረት የምታደርግበት ጊዜ አይደለምን?

ምንም አያስከፍልህም ግና ምናልባት በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የአዲስ ዘመን መጀመሪያ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፣ የሙስሊም እንኳን ቢሆን፡፡

ለማዳረስ የማይቻል ነው፡- ያን ይህ ሰው በአስራ አራተኛው ክ/ዘመን ውስጥ የሠራውን፣ 15 በጣም ታዋቂ የዓለም ሰዎችን ብቻ በማጣቀስ፣ ብሎም ይህን ሁሉ በጥቂት ስላይዶች ላይ ብቻ በማሳየት አምላክ ለዚህ ሰው በ6000+ አንቀጽ የነገረውን ፍሬ ነገር ማሸፈን አይቻልም፡፡

## በቅርብ የተገኙ መረጃዎች

ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ምዕራፍ 5 ቁጥር 16 ላይ በስም ተጠቅሰዋል፡-

***"HikkoMamittakim we kullo Muhammadim ZehdoodehwaZehraeeBayna Jerusalem."***

*"አፉ እጅግ ጣፋጭ ነው፣ እርሱም ፈጽሞ ያማረ ነው፣ እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ፣ ውዴ ይህ ነው፣ ባልንጀራዬም ይህ ነው፡፡" (መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን 5፡16)*

በዕብራይስጥ ቋንቋ ውስጥ "im" የሚጨመረው ለአክብሮት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስም በኋላ "Muhammadim" (ሙሐመዲም) ለማድረግ "im" (ኢም) ተጨምሯል፡፡ በእንግሊዘኛው ትርጉም እንኳን እነርሱ የነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስም "altogether lovely" በሚል ተርጉሞታል፡፡ ግና በእብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስም አሁንም ድረስ አለ፡፡ (እንደ ዶ/ር ዛኪር ናይክ ገለፃ፡፡)

የቱርክ ባለሥልጣናት ያ 1500 ዓመት ዕድሜ እንዳለው የሚታሰበውን አሮጌው መጽሐፍ ቅዱስ በድብቅ ቀረጥ ሳይከፍሉ ከሚያስገቡ ወንበዴዎች እጅ ከተያዘ በኋላ በደህና ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡ ይህ በአራማይክ ቋንቋ የተፃፈው አሮጌው መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ከርሱ በኋላ ስለሚመጣው ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የተናገራቸውን ትንቢቶች ይዟል፡፡

Old bible predicting Mohammed now in video! | News | MSN Arabia

News Business Entertainment More Life style Technology Autos Sports Home > News Old bible predicting Mohammed now in video! Released on - Wednesday, 29 February, 2012 -17:28 Written by Mohamed Gabal. Turkish authorities have assured that the old bible thought to be 1,500 years old is being kept safe after being seized from a gang of smugglers. The following video broadcasted by international news channel Euro news shows the Aramaic-language old bible containing Jesus prediction of Mohammed

(Peace be upon Him) coming after him. In Pictures, old Bible predicting Mohammed Watch the video: Most recent news Home News Business Entertainment Lifestyle Technology Autos Back to PC version © 2012 OTVENTURES | Hosted by LINK Datacenter

***ይህ (መልዕክት) እውነት መሆኑ እስኪገለጽላቸው ድረስ በመላው አድማስ፣ በነፍሶቻቸውም ውስጥ ተአምራቶቻችንን እናሳያቸዋለን፡፡ ጌታህ በሁሉም ነገር ላይ መስካሪ መሆኑ በቂ አይደለምን? (አል-ቁርኣን 41፡53)***

ስለዚህ እንዴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መገለጫ ከተረዳን እርሱ የተላከበትን መልዕክት መቀበል አለብን፡፡ እርሱ የተላከው ለመላው የሰው ልጆች እንደ አርአያ ነው፡፡ ከተከበረው ቁርኣን ቀጥሎ ያሉት አንቀጾች የርሳቸውን ተልዕኮ ግልጽ በሆነ አቀማመጥ ራሱን በሚያብራራ ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡-

***አንተ ነብይ ሆይ! እኛ መስካሪ፣ አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርገን ላክንህ፡፡ ወደ አላህም - በፈቃዱ - ጠሪና ብርሃን ለጋሽ መብራት (አደረግንህ)፡፡ ስለሆነም አማኞችን ከአላህ ዘንድ ታላቅ ችሮታ እንደሚጠብቃቸው አብስራቸው፡፡ (አል-ቁርኣን 33፡45-47)***

አሁን ባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመሳሳይ ሐሳብ እናገኛለን፡፡ ይህም በኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) የተነገረና ያን ከርሱ በኋላ የሚመጣውን ሰው አስቀድሞ የተነበየ ጊዜ የተናገረው ነው፡፡ እናም ይህ ሰው ያለ ምንም ጥርጥር "ሙሐመድ" ነው፡፡

***እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል፡፡ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ፡፡ እርሱም መጥቶ ስለኃጢአት፣ ስለ ጽድቅም፣ ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ ስለ ኃጢአት፣ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፣ ወደ አብ ስለምሄድ፣ ከዚህም በኋላ***

*ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርዱም፣ የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው፡፡ የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፣ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፣ የሚመጣውንም ይነግራችኋል፡፡ እርሱ ያከብረኛል፣ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና፡፡ (ዮሐንስ 16፡7-14)*

በሚያስደንቅ ሁኔታ እነዚህ ቁርኣናዊ አንቀጾችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች የኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) ትንቢት በማያጠራጥር መልኩ መፈጸሙን ያሳያሉ፡፡ እናም በዚህ አጋጣሚ የራሳቸውን ማስረጃ መያዝ ለክርስቲያኖች መሠረታዊ ግዴታ ነው፡፡ እንደዚሁም በሁለቱ ታላላቅ የአላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ነብያት (ሰላምና እዝነት በሁለቱም ላይ ይሁን) መካከል ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት ለመማር ፈቃደኝነታቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡

እንደው እንደፈጣን ማስታወሻ "ሙሐመድ" የሚለው የዐረብኛ ቃል "ያ የተከበረው" ወይም "ያ የተወደሰው" ወይም "ያ በሰፊው የተወደደ" የሚሉትን አባባሎች ይወክላል፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) በዓለም ላይ "ሙሐመድ" ተብለው ለመጠራት የመጀመሪያው ሰው ነበሩ፡፡

ከዚህ በታች ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) በዛሬው የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይህን ሰብአዊ ነብይ፣ ያን ስለመምጣቱ የተነበየለትን እንዴት እንደጠራው የምናየው ይሆናል፡፡ "ያ የተከበረው"

ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) በግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ፐሪክሊቶስ" የሚለውን የግሪክ ቃል ተጠቅሟል፡፡ ይህም የተወደደ ወይም የተወደሰ ማለት ነው፡፡ ያን ትንቢት የተነገረለትን ሰብአዊ ነብይ "ፐሪክሊቶስ" ብሎ ጠርቶታል፡፡ ይህ ቃል በዐረብኛ "ሙሐመድ" ከሚለው ቃል ጋር በትክክል ይገጥማል፡፡ ትርጉሙም

"ያ የተወደደ" ወይም "ያ የተወደሰ" ማለትን ያመለክታል፡፡ በሌላ አነጋገር "ፐሪክሊቶስ" በግሪክ "ሙሐመድ" ነው፡፡

(ምንጭ፡- www.Answering-Christianity.com)

የኔን መደምደሚያ ቀጥሎ ባለው የአል-ቁርኣን አንቀጽ፣ ያ ኢየሱስ (ዐለይሂስ ሰላም) እንዴት ከርሱ በኋላ የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መምጣትን በሁለተኛ ስሙ "አሕመድ" የሚገልጽ በሆነው ለማጠናቀቅ እወዳለሁ፡-

*የመርየም ልጅ ዒሳም "የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልዕክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደ እናንተ የተላክሁ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ" ባለ ጊዜ የሆነውን አስታውስ፡፡ ዒሳ (ሙሐመድ) በግልጽ ተዓምራቶች ባመጣላቸቸው ጊዜ "ይህ ግልጽ ድግምት ነው" አሉ፡፡ (አል-ቁርኣን 61፡6)*

የክርስትናና የኢስላም እንቅስቃሴ ምሳሌ ልክ እንደ ሁለት አትሌቶች ምሳሌ ነው፤ ሁለተኛው መሮጥ ከመጀመሩ በፊት የመጀመሪያው አስቀድሞ 600 ኪሜ ርቀት ቢሸፍንም፣ ግና በመጨረሻ ላይ ስኬታማ ሆነ፡፡ ምንም እንኳን የመጽሐፉ ባለቤቶች የነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) መገለጫዎች ለመደበቅ የራሳቸውን ከፍተኛ ጥረት ለማድረግ ቢሞክሩና ቢደክሙ፣ ኢስላም ያ እርሱ በክርስትናው ዘመን ከ600 ዓመታት በኋላ የተላከበት ሃይማኖት በዛሬው ዓለም ላይ የበላይ ሃይማኖት ሆኗል፡፡ ይህም ቀጥሎ ካለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ሊረጋገጥ ይችላል፡-

*አላህ ያ አጋሪዎች ቢጠሉም መልዕክተኛውን በመመሪያ መጽሐፍና በእውነተኛው ሃይማኖት (በኢስላም) ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ሊያደርገው የላከው ነው፡፡ (አል-ቁርኣን 61፡9)*

*“ውሸት በዓለም ዙሪያ ግማሽ መንገድ ሊሄድ ይችላል፣ ግና እውነት ጫማውን ሳያጠልቅ፡፡” (ማርክ ዌይን፣ ኦክስፎርድ ዲክሽነሪ ኦፍ ፕሮቨርብስ)*

ግና ወቅቱ የመጣ ጊዜ እውነት ውሸትን ያሸንፋል፡፡ ይህም ዛሬ በዓለም ላይ ከክርስትናና ከኢስላም ዕድገት አንፃር ምርጥ ምሳሌ መሆን ይችላል፡፡ ለዚህም ነው በ “ኢስላም ፎቢያ” (ምክንያት የለሽ ለኢስላም ያለው ጭፍን ጥላቻ) ተብዬው ለቅሶ የተሰላቸነው፡፡

***እውነትን ሐሰት ላይ በርግጥ እንጥላለን፡፡ ያፈራርሰዋልም፡፡ (ሐሰት) በባህሪው ጠፊ ነውና፡፡ እናንተ ግን - (በኛ ላይ) ለምትለጥፉት (ቅጥፈት) ወዮላችው፡፡ (አል-ቁርኣን 21፡18)***

## ማጠቃለያ

እስካሁን እንዴት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች የነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ለመላው የሰው ልጆች የመጨረሻው መልዕክተኛ የመሆናቸውን እውነተኛነት እንዳረጋገጡ በጥልቀት ተወያይተንበታል፡፡ የተደረገው ጥረት እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች፣ እነዚያ እነርሱ በማወቅ ወይም ባለማወቅ በነርሱ መጽሐፍ ውስጥ ሳያስተውሉት የቀሩት ጉዳዮች የመኖራቸውን እውነታ ወደ ክርስቲያኖች ትኩረት ለማምጣት ነው፡፡

የአይሁዶች ቀደም ሲል የተመሠረተው ማለትም እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ለማስተባበል የነበራቸው እምነትና የክርስትና ባህል በዓለም ላይ የበላይ መሆን፣ ሰዎች እውነትን እንዳይቀበሉና በእምቢተኝነት እንዲቀጥሉ ካደረጋቸው ውስጥ፣ እነዚህ የተወሰኑ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡ ወደ ኢስላማዊው ታሪክ መለስ ብለን ስንመለከት ከሁለቱም ከአይሁድና ከክርስትና ኢስላምን የተቀበሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚያ ኢስላምን የተቀበሉት እነሱ የኢስላም ነብይ እርሱ ያ በኦሪትና በወንጌል የተተነበየው እንጂ ሌላ አለመሆኑን

ያስተዋሉ ጊዜ ነበር፡፡ ለነዚያ ከሁሉም የዓለም ማዕዘን ኢስላምን እየተቀበሉ ላሉ ሰዎችም ተመሳሳይ ነገር እውነት ነው፣ እነርሱም እንደዚህ ዓይነት እውነታዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማወቃቸው ነው፡፡

***የእስራኤል ልጆች ሊቃውንት የሚያውቁት መሆኑ ለነርሱ (ለመካ ከሀዲያን) ምልክት አይሆናቸውምን? (አል-ቁርኣን 26፡197)***

*"እውነት ምናልባት ለትንሽ ጊዜ ልትጎዳ ትችላለች፣ ውሸት ግን የምትጎዳው ለዘላለም ነው፡፡"*

"እባካችሁ እውነትን ተቀበሉ!!"

***ለነዚያ በተውራትና በኢንጂል ውስጥ ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ መልዕክተኛ ለሚከተሉትም (እዝነቴን እጽፋለሁ)፡፡ (ይህ መልዕክተኛ) በመልካም ያዛቸዋል፡፡ ከክፉም ይከለክላቸዋል፡፡ መልካም ነገሮችን ይፈቅድላቸዋል፡፡ ሸክማቸውን ያራግፍላቸዋል፣ የተጫናቸውን ቀንበርም ያወርድላቸዋል፡፡ እነዚያ በርሱ ያመኑት፣ ያከበሩት፣ አጋር የሆኑትና ከራሱ ጋር የወረደውን ብርሃን የተከተሉት እነርሱ በርግጥም ስኬታማዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ (አል-ቁርኣን 7፡157)***

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) የርሱን ተወዳጅ ወይም ተመራጭ ነብይ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ባህሪያት እነዚያን በኦሪትና በወንጌል የተፃፉትን በአል-ቁርኣን ውስጥ የጠቀሰ ጊዜ እኛ ማግኘት እንደምንችል በሚገባ ያውቃል፡፡ የሙስሊም ማህበረሰብ ቀደምት ትውልድ ከቅዱስ ቁርኣን የበለጠ እውነተኛ መጽሐፍ እንደሌለ ታላቅ ግምትና እምነት ስለነበራቸው ያ የነርሱ ነብይ መምጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ እንደተጠቀሰ ለማመን ምንም ጥርጣሬ አልነበራቸውም - በዚህ መጽሐፍ ይሁን በዚያ መጽሐፍ ወይም ከመጽሐፉ በዚህ ገጽ ይሁን በዚያ ገጽ ያ የነርሱ ችግር አልነበረም፡፡ ለነርሱ ጠንካራ እምነት ባይሆን ኖሮ እነርሱ

ከመጽሐፉ ባለቤቶች ጋር የቃላት ጦርነትን ለማስወገድ የዚህን ዓይነት ጠቋሚ አንቀጾች ከአል-ቁርኣን ውስጥ ይሰርዙ/ያጠፉ ነበር፤ ምክንያቱም በቦታው ላይ እንደ ሼኽ አሕመድ ዲዳት ዓይነት ሰዎች ስላልነበሩ እነርሱ ለምሳሌ ያህል ኦሪት ዘዳግም 18፡18 ወይም ትንቢተ ኢሳይያስ 42፣ ወዘተ ብለው መጥቀስ አይችሉም ነበር፡፡

በኢስላምና ክርስትና መካከል የምርምርና ጥናት ዕድገት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ዐረብኛ መተርጎም፣ በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል የተደረጉ ውይይቶች፣ አሁን እንደሚታየው ከክርስትና ወደ ኢስላም የተመላሾች፣ በተለይ እነዚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ምርጥ ዕውቀት ያላቸው ተመላሾች ቁጥር መጨመር፣ እነዚህ ያን የመጽሐፉ ሰዎች የደበቁትንና ያስተባበሉትን እውነታ በቅርቡ አጋልጧል፡፡ ለዚህና ለመጪው ትውልድ፣ መንገዱ በመጠረጉ ስለኢስላም ነብይ የተነገሩትን ትንቢቶች ለመተርጎም ምንም ግራ መጋባት አይኖርም፡፡

ስለዚህ ማንኛውም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸ ትንቢት የነብዩ ሙሐመድን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስብዕና/ማንነት በመግለጽ ረገድ ከአል-ቁርኣንና ከሐዲሥ ጠንካራ ድጋፍ አለው፡፡ ይህ መገጣጠም እንዲሁ በአጋጣሚ የሆነ አይደለም፡፡ ግና ይህ በዕቅድ አውጪው ቀደም ተብሎ የተቀረጸ፣ ያ ከርሱ በፊት የነበሩትን መልዕክተኞች ሁሉ በላከውና እነርሱም ስለመጨረሻው ነብይ፣ ስለዚያ ለመላው የሰው ልጆች እንደ እዝነት ሆኖ ከእስማዔል ዝርያዎች የሚመጣ ስለሆነው ስለርሱ የራሳቸውን ሕዝቦች እንዲያስተምሩ ደንግጓል፡፡

እናንተም የቀረቡትን እውነታዎች ከተረዳችሁና እውነታውን ከተቀበላችሁ፣ ይህ እናንተን የበለጠ የሚያነሳሳው ወይም እንደ ምንዳችሁ ይሆን ዘንድ ከጌታችሁ የተገባላችሁ የተስፋ ቃል ነው፡-

*(የ)ተውራትንና (የ) ኢንጂልን (ትዕዛዛት)፣ ከጌታቸው የተወረደላቸውንም (መልዕክት) በትክክል ቢተገብሩ ኖሮ ከበላያቸውም ከበታቻቸውም በተመገቡ (የተትረፈረፈ ሲሳይ በተለገሳቸው) ነበር፡፡ ከነርሱ ውስጥ ቅን የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡ ግና ብዙዎቹ ምግባራቸው እጅግ አስከፊ ነው፡፡(አል-ቁርኣን 5፡66)*

አሊያም ምናልባት እናንተ በራሳችሁ መጽሐፍ ውስጥ፣ ያንን የተጠቀሰውን የአላህን ባሪያ እንድትቀበሉ የሚጋብዛችሁን፣ ወይም ያን ያልተማረንና የማያነብን ነብይ፣ ያን እናንተ በመጽሐፋችሁ ውስጥ ተጽፎ የምታገኙትን ሳታስተውሉ ከቀራችሁ በናንተ ላይ የሚያስከትለው ውጤት በቁርኣንም እንደሚከተለው ተጠቅሷል፡-

*ከኢስላም ውጭ ሌላን ዲን (የሕይወት መመሪያ) የሚሻ ሰው ከርሱ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ እርሱም በመጭው ዓለም ከከሳሪዎች ነው፡፡ (አል-ቁርኣን 3፡85)*

*እናንተ ደንቆሮዎች ስሙ፤ እናንተም ዕውሮች ታዩ ዘንድ ተመልከቱ፡፡ (ኢሳይያስ 42፡18)*

*በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ፡፡ (ዘዳግም 18፡18)*

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ)፣ ኃያሉ አምላክ፣ በመጽሐፉ ባለቤቶች ላይ የርሱን የመጨረሻ ነብይ የመግለጽ፣ በመጻሐፋቸው ውስጥ እንዲጠብቁና ለሰው ልጅችም ግልጽ እንዲያደርጉ ሆን ብሎ ታላቅ ኃላፊነትን አሸክሟቸዋል፡፡

*አላህ ከነዚያ መጽሐፉ ከተሰጣቸው ወገኖች ፡- "ለሰዎች ልታብራሩትና ልታስተምሩት፣ ላትደብቁትም" ቃል ኪዳንን በያዘ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡፡ (ይህን ቃል ኪዳን) ወደኋላቸው አሽቀንጥረው ጣሉት፡፡ በርሱ ጥቂቱን ዋጋ ሸመቱበትም፡፡ የሸመቱት ነገር ምን ያህል አስከፊ ነው! (አል-ቁርኣን 3፡187)*

ስለዚህ፣ ያ ነበር ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)፣ ለመላው የሰው ልጆች የእዝነትና የመድኅን ነብይ፣ ያ የርሱ መንገድ በመጀመሪያ እርከን የተሳለቁበት፣ በሁለተኛው እርከን በኃይለኛው የተዋጉት፣ ግና በሦስተኛው እርከን ራሱን በቂ ማስረጃ ሆኖ የተቀበሉት፡፡ ሆኖም ግን አብዛኛው ሰው ይህን አያውቅም፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ሙስሊሞች እርሳቸውን ከማክበር፣ ከመታዘዝና እርሳቸው ያስተማሩን ሕጎችና ደንቦች ከመተግበር ውጭ እርሳቸውን ፈጽሞ ወደ መለኮታዊነት ደረጃ ከፍ አላደረጉትም፡፡ ስለሆነም የእምነታችን መሠረት ከአላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) በስተቀር በሐቅ የሚመለክ እንደሌለና ሙሐመድም (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የርሱ ባሪያና መልዕክተኛው መሆናቸውን መመስከር ነው፡፡

# ተፈጸመ

## ዋቢ መጽሐፍት


1. ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ መልዕክተኛ፣ በዐብዱር-ረሕማን አሽ-ሼሃ፣ 2005 እ.ኤ.አ
2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለሙሐመድ ምን ይላል? በሼኽ አሕመድ ዲዳት
3. የነብዩ ሶላትና ውዱእ www.islamhouse.com
4. ሙሐመድ፣ ለመላው የሰው ልጆች የአምላክ ነብይ፣ በሙሐመድ ኤል ሐጅ መሕሙድ ጣሊብ፣ 2006 እ.ኤ.አ
5. የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው መልዕክት፣ በዶ/ር ቢላል ፊሊጽስ
6. ሙሐመድ፣ ልክ አንተ እንደምታየው፣ በዓእድ አል-ቀርኒ፣ 2008 እ.ኤ.አ
7. የሙሐመድ ነብይነት እውነታ ወይስ አፈታሪክ፣ በዐብዱር-ረዲ ሙሐመድ ዐብዱል ሙሕሲን፣ 2006 እ.ኤ.አ
8. መስቀሉና ጨረቃው፣ በጌራልድ ኤፍ.ዲርክስ፣ 2008 እ.ኤ.አ
9. ንግግሮች ለሚመራመር አዕምሮ፣ በኢምትያዝ አሕመድ፣ 2000 እ.ኤ.አ
10. በማደግ ያለ ሃይማኖት፣ ኢስላም በሦስተኛው ሚሌኒየም፣ በሙራድዊልፍሪድ ሆፍማን፣ 2001 እ.ኤ.አ
11. ኢስላምና ዓለም፣ በዐብዱልሐሰን አሊ ነድዊ፣ 2006 እ.ኤ.አ
12. ነብዩ ሙሐመድ፣ ለሰው ልጆች በረከት፣ ዓለም አቀፍ ኢስላማዊ ማተሚያ ቤት፣ 2004 እ.ኤ.አ
13. ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ በዶ/ር ጀማል በደዊ
14. ክቡር ቁርአን፣ የአማርኛው ትርጉም፣ ነጃሺ ማተሚያ ድርጅት ያሳተመው፣ 11 ጥራዞች
15. ሰሒሕ አል-ቡኻሪ የእንግሊዘኛ ትርጉም